# መጽሔተ ተልእኮ

## ዘማኅበረ ቅዱሳን




ሰኔ
፳፻፲፯

ሁለተኛ
ዕትም

አዘጋጅ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት
ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን
የሕዝብ ግንኙነትና ትብብር አገልግሎት ማስተባበሪያ

# መጽሔተ ተልእኮ

## ዘማኅበረ ቅዱሳን



ሰኔ
፳፻፲፯

ሁለተኛ
ዕትም

ማኅበረቅዱሳን በማእከላት
(የሰቆጣ ማእከል)





መምህር ዲያቆን ደምስ

አዘጋጅ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት
ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን
የሕዝብ ግንኙነትና ትብብር አገልግሎት ማስተባበሪያ

# ማ ው ጫ


01 መልእክት ዘማኅበረቅዱሳን

02 ትምህርተ ወንጌል

03 ግብረ ማኅበረ ቅዱሳን

04 ማኅበረ ቅዱሳን በማእከላት

05 ቤተ አናግድ

06 ይናገራል ፎቶው

## 1. መልእክት ዘማኅበረቅዱሳን

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!**

ማኅበራችን ማኅበረ ቅዱሳን ከሦስት አሥርት ዓመታት በላይ በዘለቀው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት "ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።" ሮሜ 12፥1 የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስ ቃል የአገልግሎቱ መመርያ በማድረግ በገጠር፣ በከተማ፣ በሀገር ውስጥም፣ ከሀገር ውጭም በክርስትና ያጌጡ፣ በቅድስና መዓዛ የተሳቡ፣ የቤተ ክርስቲያን ፍቅር በልባቸው የሚቀጣጠል፣ የቅዱሳን ወዳጅ፣ ጨው ሆነው አልጫውን ዓለም በወንጌል ጨው ያጣፈጡ አገልጋዮችን ማፍራት ተችሎአል። አገልግሎት አድማሱንም በማእከላት፣ በወረዳ ማእከላት፣ በግንኙነት ጣቢያዎችና በግቢ ጉባኤያት በሀገር ውስጥና በማእከላት፣ በንዑሳ ማእከላት፣ ግንኙነት ማእከላትና በግቢ ጉባኤያት በውጭ ሀገር በማስፋፋት ላይ ይገኛል።

በመላው ዓለም የሰፋው ይህ አገልግሎት ዘር፣ ቋንቋ፣ ቀለም ሳይለይ ሞገሳችን፣ ክብራችን፣ የዓለም ጌጥ፣ የጥበብ መገኛ፣ የሕይወት ምንጭ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን በመስበክ ወደ ቤተ ክርስቲያን ኅብረት እየጨመረ ይገኛል። የክርስቶስ ወንጌልንም ስናስብ "ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም" እንዳለ ጌታችን (ማቴ 10፥ 37) ኢየሱስ ክርስቶስን ስንከተል፣ በስሙ ስንጠራ ከእናት ከአባት ከእኅት ወንድም መለየትን የሚጠይቅ ነው። በዘማናችን ደግሞ ከዚህ ወርደን በብሔር፣ በቋንቋ፣ በነገድ ተከፋፍለን ክርስቶስን እናመልካለን በእርሱም ስም እንጠራለን ማለት በወንጌል መዋሸት ስለሚሆንብን እግዚአብሔርን አስቀድመን በወንጌል መመርያነት አገልግሎታችንን የተቀደሰ መስዋዕት አድርገን እንድናቀርብ መልከታችን ነው።

የተወደዳችሁ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ይህ ወቅት ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት በኋላ ቅዱሳን ሐዋርያት ጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ለአገልግሎቱ ሁሉ መጀመሪያና መሠረት አድርገው የጾሙትን ጾም እኛም እግዚአብሔር በሕይወታችን የጨመረልን መልካም ሥጦታ እንደመሆኑ ኃጢአቱን እንደ ሚያስተሠርይ እንደ ሚጾምና እንደ ሚጸልይ ጥበበኛ ሰው በጥበብ እየተመላለስን ነፍሳችንን በአገልግሎቱ በረከት እያለመለምን ኃጢአታችን ለአገልግሎት እንቅፋት እንዳይሆንብን ከምንጊዜውም በላይ ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት ምሕረትን የተሞላች የእጁን በረከት የምንናፍቅበት ጊዜ እንዲሆንልን ከልብ እንመኛለን።

ማኅበራችን ማኅበረ ቅዱሳን አሠራሩን በማዘመን ዘመኑን በመዋጀት የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነ ሲሆን በሕዝብ ግኙነትና ትብብር አገልግሎት ማስተባበርያ በእየሦስት ወሩ እየተዘጋጀች የተለያዩ አምዶችን በመያዝ ወደ እናንተ የምትደርሰው መጽሔተ ተልእኮ ማኅበሩ እንዲከናወን የሚፈልገውን መለእክት፣ እያከናወናቸው ያሉትን መንፈሳዊና ልማታዊ ሥራዎች ፊትን እንደሚያሳይ መስትዋት ማኅበራችንን በጥቂቱ የምናይባት መስትዋት ሆና ቀርባልናለችና ትኩረት ሰጠተን በማንበብና የያዘቻቸውን መልእክቶች በመተግበር ተወዳች ሆና እንድትቀጥል ሀሳብ አስተያየታችሁን እንድታካፍሉን ለማሳሰብ እንወዳለን።

በመጨረሻም “በሥላሴ ገመድ ታሥርን ባማይለያይ ሰንሰለቱም ታተምን ከልቦናዎቻችን በማይነቀሉ የፍቅሩ ችንካሮች ተቸነከርን ያዝነው አንለቀውም እርሱም አቀፈን አልተወንም ወደ እርሱም በሃይማኖት አቀረበን ከእርሱም ወደ ቀኝ ወደ ግራ አንሸሽም እንደ ቀለበት በልባችን እንደ ማኅተም በክንዳችን አኖርነው ፍቅሩ በልባችን ሞልቷልና እንዳለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በሃይማኖት ጸንተው በምግባር ቀንተው በሰማዕትነት ለአረፉት ወገኖቻችን እረፍተ ነፍስን እንዲሰጥልን አምላካችንን እየለመንን በእየ ጊዜው በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰውን አስቃቂ ግድያ ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኝ ሁላችንም ባለ ድርሻ እንድንሆን መልእክታችንን እንስተላልፋለን።

ይህ መጽሔት አምስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የማኅበሩን አገልግሎቶች በተለያዩ ክፍሎችና ሁኔታዎች ከፋፍሎ በውስን መልኩ ያሳያል። በተቀደሰ ወንጌል ነፍሳችንን የሚያለመልም ትምህርት ቀርቧል፤ የማኅበሩ የስድስት ወር የአገልግሎት አፈጻጸም ዝርዝር ሪፖርት በተብራራና ግልጽ በሆነ መልኩ ተካቷል፤ ማኅበረ ቅዱሳን በሰቆጣ ማእከልን ከምሥረታው አንሥቶ አሁን እስካለበት ድረስ ያለውን ሰፊ ጉዞ በመጽሔቱ እንመለከታለን፤ ከነባርና ፈር ቀዳጅ ከሆነ አገልጋዮች መካከልም መምህር ደምስን ማኅበረ ቅዱሳን ከአጀማመሩ አንሥቶ ያለውን ተጠይቀው ያሉትን እናነባለን፤ በመጨረሻም ከጠረፋማ አካባቢዎች በመምጣት በተለያዩ አድባራት የሠለጠኑትን አገልጋዮች በፎቶ እንቃኛለን! መልካም ንባብ!

## 2. ትምህርተ ወንጌል

<<. . .አሁንም በፍጹም ልቡናህ ጨክነህ ንስሐ ግባ. . .>> (፪ኛ መቃ ፲፥፮)

ንስሓ ማለት አንድ ክርስቲያን ከክርስትና ጥምቀት በኋላ በድካም ወይም ባለማወቅ ለፈጸመው ኃጢአት በፈጣሪው ፊት ቀርቦ የሚጸጸትበት፣ ዳግመኛ ያን ኃጢአት ላለመሥራት ወስኖ በመናዘዝ ከእግዚአብሔር ጋር የሚታረቅበትና የነፍስ ፈውስ የሚያገኝበት ታላቅ ምሥጢር ነው። የሰው ልጅ ከኃጢአት ያለ ንስሓ ንጹሕ ሊሆን ስለማይችል ንስሓ የሌለበት ሕይወት መጨረሻው ጥፋት ነው።

ንስሓ በስሜታዊነት የምንገባው ሳይሆን በፍጹም ጸጸት፣ በመመለስና በማመን በካህኑ አማካይነት በእግዚአብሔር ፊት የምንፈጽመው ከኃጢአት፣ ከበደል፣ ከዲያብሎስ እስረኝነት የምንላቀቅበትና የምንነጻበት ድንቅ ምሥጢር ነው። ተወዳጁ ሐዋርያ ቅዱስ ዮሐንስ በመልእክቱ "ኃጢአት የለብንም ብንል ግን ራሳችንን እናስታለን፤ የቀና ነገርም በእኛ ዘንድ የለም።" (፩ኛ ዮሐ ፩፥፰) ብሎ እንደነገረን ከበደል ነጻ ነን በማለት ራሳችንን ማታለል ለንስሓ እንዳንበቃ ያደርገናል፤ ሰው ከገቢር ኃጢአት ቢጠበቅ ከነቢብ አይነጻም፣ ከነቢብ ቢጠበቅ ከኀልዮ ኃጥአት አይነጻምና ንስሓ ለሰው ልጅ መሠረታዊ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኛ ድልድይ ነው።

እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ሰዎች በንስሓ ወደእርሱ እንዲመለሱ ጥሪ በማድረግ ይጠባበቃል፤ ፈቃዱንም እንድናደርግ እርሱም ምሕረቱን ሊያወርድልን መልካምና በጎ ፈቃዱ ነው፤ "ወደ እግዚአብሔር ተመለስ፥ ኃጢአትንም ተዋት፤ በፊቱም ጸልይ፤ ለበደልህም ንስሓ ግባ፤ ከበደልህም ወደ እግዚአብሔር ተመለስ፤ ኃጥአትን ሁሉ ጥላ፤ ፈቃዱንም አድርግ።"(ሲራክ ፲፯፥፳፭-፳፱) በማለት ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚነግረን በንስሓ ሕይወት የመኖር ጥበብን ገንዘብ አድርጎ ወደ እግዚአብሔር በመመለስ በፈቃዱ መመላለስ ምሕረቱን ቸርነቱን ያጎናጽፋል።

ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚመሰክሩልን ንስሓ የሰው ልጅ ከውድቀት ተነሥቶ ከፈጣሪው ጋር የሚታረቅበት ብቸኛ መንገድ ንስሓ ነው። በመጽሐፈ መቃብያን ላይ እንደተጠቀሰው "በንጹሕ የሚለምኑትን ሰዎች ፈጽሞ ይወዳቸዋል፤ ጸሎታቸውንም ይሰማቸዋል፤ ጨክነውም ንስሓ የሚገቡትን ሰዎች ንስሓቸውን ይቀበላቸዋል፤ ሥርዓቱንና ሕጉን ትእዛዙንም ለሚጠብቁ ሰዎች ጽናትና ኃይልን ይሰጣቸዋል" (፪መቃ.፳፩፥፳፯)። ይህ ቃል የሚያስገነዝበን ንስሓ የእግዚአብሔርን ቸርነት የምንቀበልበት ቁልፍ ምሥጢር መሆኑንና እግዚአብሔርም በንስሓ ለሚኖሩ ሰዎች ቅርብ መሆኑን ነው።

በተቃራኒው ንስሓን ችላ ማለት ግን ከቀድሞው በደል የከፋ ጥፋት እንደሚያመጣ ቅዱስ መጽሐፍ ያስጠነቅቀናል፤ "በድሎ በ ንስሓ የማይመለስ ሰው ከቀድሞ በደሉ ይልቅ በደልን አብዝቷል፤ አንተ ግን በልብህ ትዕቢት በንስሓ መመለስ ተሳነህ" (፫መቃ.፬፥፴፪) ስለሆነም "ያለ መከራና ያለ ደዌ በተድላና በደስታ ትኖሩ ዘንድ ዘመናችሁ ሳያልፍ ባለ ዘመናችሁ ንስሓ ግቡ እንጂ ከሞታችሁ በኋላ ያለፈው ዘመናችሁ አይመለስምና አልቅሱ" (፫መቃ. ፮፥፳) ተብሎ እንደተጻፈ ጊዜው ሳይረፍድብን ዛሬውኑ ወደ ንስሓ መቅረብ ይገባናል።

እውነተኛ የንስሓ በረከትን ለማግኘትና ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ የሚከተሉትን ነጥቦች ማሟላት ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም፦

ሀ) ልባዊ ጸጸት፦ በበደላችንን፣ እግዚአብሔርን ማሳዘናችንን ተረድተን ከልብ በሆነ ጸጸት ማዘን ያስፈልጋል፡፡ ይህም እንደ ቅዱስ ዳዊት ማቅ በመልበስ፣ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ጥልቅ ዕንባን በማፍሰስና እንደ ሕዝቅያስ በጥልቅ የመመለስ ጸጸት የታጀበ ሊሆን ይገባል።

**ለ) ጽኑ ውሳኔ፦** ዳግመኛ ወደ ኃጢአቱ ላለመመለስና በደሉን ላለመድገም በቁርጠኝነት መወሰን ይጠበቅብናል፡፡

ሐ) ከወንድም ጋር መታረቅ፦ በሰዎች መካከል ቅሬታ ካለ ንስሓ ከመግባታችን በፊት ዕርቀ ሰላም ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

**መ) ግልጽ ኑዛዜ፦** ኃጢአታችንን ሳንደብቅ ለንስሓ አባት (ለካህን) አንዳች ሳናስቀር በዝርዝር መናገር፤ “የሠራውን ኃጢአት ይናዘዛል...ካህኑም ስለ ኃጢአቱ ያስተሰርይለታል። እርሱም ይቅር ይባላል” (ዘሌ.፭፥፭፲) ሐኪም የታመመውን ቁስል ካላየው ፈውስ መስጠት እንደማይችል ሁሉ፣ ካህኑም በኑዛዜ ያልተነገረን ኃጢአት ሊያከመው አይችልም። “ኃጢአቱን የሚሠውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል” (ምሳ፳፰፥፲፫) ቅዱስ ያዕቆብም “እርስ በርሳችሁ በኃጢአታች ሁ ተናዘዙ፤ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ” (ያዕ. ፭፥፲፮) በማለት የኑዛዜን አስፈላጊነት አስተምሮናል።

***ሠ) ቀኖናን መፈጸም፦*** ከካህኑ የሚሰጠውን ቀኖና (መንፈሳዊ መድኃኒት) በደስታና በትሕትና ለመቀበልና ለመፈጸም ዝግጁ መሆን ማለት ነው፡፡ በእነዚህም መሠረታዊ ሂደቶች በመጓዝ በካህናት በኩል ከእግዚአብሔር ምሕረትን እናገኛለን።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት “ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ም ተይዞባቸዋል” (ዮሐ. ፳፥፳፫) በማለት የሰጠው ሥልጣነ ክህነት በምድር የሚፈቱት በሰማይ የተፈታ እንዲሆን ያደርጋል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም “እግዚአብሔር ለካህናት የሰጣቸው ሥልጣን መላእክት እንኳን የሌላቸው ነው፤ እነርሱ በምድር ያስሩታል እግዚአብሔር በሰማይ ያስረዋል፤ እነርሱ በምድር ይፈቱታል፤ እግዚአብሔር በሰማይ ይፈታዋል” እንደነገረን።

በንስሓ ጉዞ ውስጥ አንዳንዶቻችን "ንስሓ መግባት እፈልጋለሁ፤ ግን ልቤ አልጸጸት አለኝ" ወይም "አንድን ኃጢአት ደጋግሜ እሠራዋለሁና ንስሓ መግባት ሰልችቶኛል" በሚል ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ልንወድቅ እንችላለን። ነገር ግን ንስሓ ከስሜት በላይ "ውሳኔ" መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል። ለዚህና ለመሰል የሚያጋጥሙ ፈተናዎች መፍትሔዎቻቸው፡-

**ሀ) በጸሎት የተሰበረ ልብን መለመን፡-** "አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ" (መዝ፶፥፲) እያልን ልብን ማለስለስ የሚችለውን ፈጣሪ ልባችንን እንዲያነጻልንና ትሑት እንዲያደርግልን መለመን ይገባል።

**ለ)** የእግዚአብሔርን ቸርነት **ማሰብ፡-** እየበደልነው ለንስሓ የሰጠንን ጊዜና ቸርነቱን በማሰብ ወደ ፍቅሩ መቅረብ ያስፈልጋል።

ሐ) ከንስሓ አባት **አለመራቅ፡-** "ልቤ ደርቋልና ምን ላድርግ?" ብለን በማማከር በምሥጢረ ንስሓ ውስጥ የሚገኘውን ጸጋ ያጣን እንዳንሆን በምክረ ካህን ልንታገዝ ይገባል።

**መ) የእግዚአብሔርን ቃል መስማትና ምጽዋት ማድረግ፡-** ቃለ እግዚአብሔር ልብን ያለሰልሳል፤ ለሰው የምናሳየው ርኅራኄ ደግሞ የፈጣሪን ርኅራኄ ያቀዳጀናልና ጥዑም ከሆነው ቃሉ ዘወትር አለመራቅና በተሰበረ ልብ እግዚአብሔር እንዲያስተምረን መማጸን ይገባል። እነዚህን ነገሮች ዘወትር እያደረግን ከንስሓ አባቶቻችን ጋር የምንነጋገር ከሆነ እግዚአብሔር ብርሃኑን ያበራልናል፤ ከኃጥአት ድቅድቅ ጨለማም እንርቃለን፤ እንጠበቃለንም።

ስለዚህ ወዳጆቻችን ሆይ! "አልለወጥም" የሚለው ፍርሃትና ተስፋ መቁረጥ ከሰይጣን እንጂ ከእግዚአብሔር አይደለም። እግዚአብሔር "የድንጋዩን ልብ አወጣለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣቸዋለሁ" (ሕዝ. ፲፩፥፲፱) ያለን ጌታ ስለሆነ ዛሬውኑ በፊቱ ተንበርክከን የጸጋ ልብ እንዲሰጠንና በንስሓ እንድንታደስ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን!

ስብሐት ለእግዚአብሔር!

## 3. ግብረማኅበረቅዱሳን

### የማኅበረ ቅዱሳን የ፫ኛው ዙር ስልታዊ  ዕቅድ የ፳፻፲፰ ዓ.ም በ፮ ወራት ውስጥ የተከናወኑ ዐበይት ተግባራት

**መግቢያ**

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን፣ "ተልእኮአችንን ለትውልድ" በሚል መሪ ቃል የነደፈውን የ፫ኛው ዙር ስልታዊ ዕቅድ (Strategic Plan) መሠረት በማድረግ የ፳፻፲፰ ዓ.ም የመ ጀመሪያ ዙር የ፮ ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርቱን በየማስተባበሪያው እንደሚከተለው ቀርቦል፡፡

**፩. የግቢ ጉባኤያት አገልግሎት ማስተባበሪያ በ2018 ዓ.ም በ6 ወራት ውስጥ የተከናወኑ ዐበይት ተግባራት**

- በግቢ ጉበኤያት አገልግሎት ማስተባበሪያ በ6 ወር የተከናወኑ አበይት ጉዳዮች
- ከግቢ  ጉባኤያት አገልጋይ ተማሪዎች መካከል 3046 አዳዲስ መምህራን በደረጃ አንድ ሥልጠና ማፍራት ተችሏል።
- ከግቢ ጉባኤያት 3439 ተተኪ አመራር በደረጃ አንድ ስልጠና ወስደዉ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛል።
- ከጠረፋማ እና አገልጋይእጥረት ካለበት አካባቢ ለመጡ 449 የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች ተልዕኮ ተኮር ስልጠናዎች ተሰጥተዋል።
- ግቢ ጉባኤያት የሚያስተምሩ 396 አዳዲስ መምህራን ከጉባኤ ቤቶች ፣ከአጥቢያ ቤ/ክ፣ከሰንበት ትምህርት ቤቶች እና አዳዲስ አባላትን በማሰልጠን ለአገልግሎት መጠቀም ተችሏል።
- በሃገር ዉስጥ ግቢ ጉባኤያት 7987 ተማሪዎች አብነት እየተማሩ የሚገኝ ሲሆን ባለፉት 6 ወራት 241 ተማሪዎች በአባቶች ቡራኬ ዲቁና እንዲቀበሉ ተደርጓል።
- ለተመረጡ 3357 የግቢ ጉባኤያት ሴት ተማሪዎች ሴቶች በኦርቶዶኪሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እና የሴቶች ማህበራዊ ከህሎት በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ተልእኮ ተኮር ስልጠና ተሰጥቷል።
- የተከለሰዉ ስርአተ ትምህርት በሁሉም የሀገር ዉስጥ ግቢ ጉባኤያት እየተተገበረ ይገኛል።
- ለ1118 የግቢ ጉባኤያት ተመራቂ ተማሪዎች በህዝብ አስተዳደር ፣ስራ ፈጠራ፣የንግድ ስራ፣የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ርዕሰ ጉዳዮች የተልዕኮ ስልጠናዎች ተሰጥቷል።

- 28 የሃገር ዉስጥ ግቢ ጉባኤያት በአካባቢያቸዉ ለሚገኙ የቤተ ክርስቲያን አካላት፣ለአካባቢ ማህበረሰብ፣ለገዳማት እና ጉባኤ ቤቶች ፣ለነዳያን ወ.ዘ.ተ የተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች እና ድጋፎች አድርገዋል (ማብላት እና ማልበስ፣ገዳማት እና ጉባኤ ቤቶችን በገንዘብና በዓይነት መደገፍ፣ሰብል መሰብሰብ፣አካባቢን የማፅዳት ስራዎች።
- በተከለሰዉ ሥርዓተ ትምህርት መሰረት 10 የኮርስ መጻሕፍት የታተሙ ሲሆን በቁጥር 13269 የሚሆኑ መጻሕፍት ለግቢ ጉባኤያት እንዲደርሱ ተደርጓል።
- ቅድመ ግቢ ዲቁና ተቀብለዉ ለገቡ 1975 ዲያቆናት ተልዕኮ ተኮር ስልጠና በመስጠት ወደ አገልግሎት እንዲሰማሩ ተደርጓል።
- ለግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች በድህረ ገፅና በጉባኤ ቃና አማካኝነት ወቅታዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች፣ መረጃዎችና የአገልግሎት ተሞክሮዎች እንዲደርሳቸዉ ተደርጓል።
- 4 አዳዲስ ግቢ ጉባኤያት እንዲመሰረቱ ተደርጓል።
- በግቢ ጉባኤያት መምህራን ማፍሪያ እና ቨርቿል ማእከል ማቋቋሚያ ፕሮጀክት አማካኝነት ለግቢ ጉባኤያት 7 መምህራን በቋሚ ተቀጥረዉ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ።
- ለ134 የግቢ ጉባኤያት ንስሐ አባቶች ተልዕኮ ተኮር የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠና ተሰጥቷል።

**፪. በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ አገልግሎት በ2018 ዓ.ም በ6 ወራት ውስጥ የተከናወኑ ዐበይት ተግባራት**

- ❖ ስብከተ ወንጌል አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ በመሠረታዊ የርቀት ትምህርት መርሐ ግብር በአማርኛ እና ኦሮምኛ ቋንቋዎች 729 ሰዎችን ማስተማር
- ❖ በስብከተ ወንጌል እና ሐዋርያዊ አገልግሎት የሚሰማሩ 1011 አገልጋዮችን ማሠልጠን እና ማሰማራት
- ❖ የስብከተ ወንጌል አገልግሎትን ተደራሽ በማድረግ ምእመናንን ለማጽናት፣ ጠፉ ወገኖችን ለመመለስ እና ቅዱስ ወንጌል ያልደረሳቸውን ወገኖች ተደራሽ ለማድረግ በልዩ ልዩ አካባቢዎች 177 ትምህርታዊ ጉባኤያት በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ተከናውነዋል፡፡
- ❖ በ10 ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የነገረ ድኅነት ቡክሌት እና በሦስት ቋንቋዎች (በወላይትኛ፣ጋሞኛ እና ሲዳምኛ ቋንቋዎች) የውዳሴ ማርያም ጸሎት መጽሐፍ ትርጉም ታትሞ ለስርጪት በቅቷል፡፡
- ❖ የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ወንጌል ተደራሽ በማድረግ 29 741 አዳዲስ አማንያን ሥርዓተ

ጥምቀት ተፈጽሞላቸው የቅድስት ሥላሴ ልጅነትን እንድያገኙ ተደርጓል፡፡

- ለአዳዲስ አማንያን መገልገያነት ሦስት አብያተ ክርስቲያናት ሕንጻ በመታነጽ ላይ ይገኛሉ፡፡
- በካህናት እጥረት ለተዘጉ 20 አብያተ ክርስቲያናት እና ለሐዋርያዊ ተልእኮ ማስፋፊያነት ለታነጹ 15 አብያተ ክርስቲያናት አገልጋይ ካህናትን በመቅጠር ለምእመናን አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡
- የስብከተ ወንጌል አገልግሎትን ለዓይነስውራን ተደራሽ ለማድረግ የነገረ ድኅነት ቡክሌት በአማርኛ ቋንቋ በብሬይል ታትቶ የማሰራጨት ሥራ ተሠርቷል፡፡

**፫. በሙያ፤ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት በ2018 ዓ.ም በ6 ወራት ውስጥ የተከናወኑ ዐበይት ተግባራት**

- ለአምስት ነባር እና ለሦስት አዳዲስ የሕፃናት ማሳደጊያዎች ድጋፍ ለማድረግ የተያዘው ዕቅድ **50**% አፈጻጸም ላይ ይገኛል።
- ሁለት የወጣቶች ማገገሚያ ማእከላት እንዲቋቋሙ ድጋፍ ተደርጓል።
- በችግር ውስጥ ለሚገኙ ወገኖችና ለተጎዱ አብያተ ክርስቲያናት የሚውል የገንዘብና የቁሳቁስ ማሰባሰብ ሥራዎች ተከናውነዋል።

**፬. በዜማና ኪነጥበባት ማዕከል በ2018 ዓ.ም በ6 ወራት ውስጥ የተከናወኑ ዐበይት ተግባራት**

1. የግእዝ ቋንቋን ለማስፋፋት የመሠረታዊ ግእዝ ቋንቋ ትምህርት በ፲፰ ክፍሎች ተዘጋጅቶ በዩቲዩብ ለተመልካች ቀርቧል።
2. በዋና ማእከልና በተለያዩ ማእከላት በመዝሙርና በዜማ መሣሪያዎች በመስቀል ከ9000 በላይ እንዲሁም በጥምቀት ከ10000 በላይ መዘምራንን በማሰለፍ አገልግሎት ተፈጽሟል፡፡
3. በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ባለፉት ስድስት ወራት ከ1000 በላይ የዜማ መሣሪያዎች ሠልጣኞችን በማስተማር ምዘና እንዲያኙ ተደርጓል፡፡
4. የዜማ መሣያዎችን ሥልጠናና ምዘና ወጥነት ለማጠናከር ማስፈጸሚያ ሰነድ ተዘጋጅቷል፤ የvertual ሥልጠና ለማስጀመር የሥልጠና ድረ ገጽ (ፕላትፎርም) በሂደት ላይ ነው።

6. 60 በላይ ለሆኑ ከተለያዩ ማእከላትና ወረዳ ማእከላት ለተውጣጡ የዜማ መሣሪያ አሠልጣኞች ተከታታይ የአሠልጣኞች ሥልጠና እየተሰጠ ነው፡፡

- ✓ የመዝሙር ሥርዓትን በተመለከተ ለሰ/ትቤቶች፤ ለግቢ ጉባኤያት፤ ለማኅበራትና ለግል ዘማሪያን እንዲሁም ከተለያዩ አኀጉረ ስብከት ለተውጣጡ ከ100 በላይ ለሆኑ አገልጋዮች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

7. ከ200 በላይ የበገና መሰንቆና ዋሽንት አገልጋዮች የሚሳተፉበት የበገና ምሽት መርሐ ግብር ተካይዶል፡፡
8. የ6 አልበም መዝሙራት በኽምጣንኛ ቋንቋ ቀረጻ ሥራ ተከናውኗል
9. የ6 አልበም በቡርጅኛ ቋንቋና 6 አልበም በአዊኛ ቋንቋ እንድሁም የሞስየኛ ቋንቋ የቅንብር ሥራ ተከናውኗል።
10. በደብረ ማርቆስ ማእከል አስተባባሪነት 2 አልበም መዝሙራት ተሠርተዋል

፫. የማእከላት አገልግሎት ማስተባበሪያ የተከናወኑ ዓበይት ተግባራት

- ❖ በየወሩ ለማእከል አመራር እና አካላት የዕቅበተ አእምሮ ስልጠና ተሰጥቷል
- ❖ የሀገር ዉስጥ ማእከላት እና 4 የዉጭ ማእከላት ቅኝት ተደርጓል፣ ግብረ መልስ በፅሁፍ ተይዟል።
- ❖ ለ800 አዳዲስ መሪ አመራር በቨርቿል ስልጠና ተሰጥቷል።
- ❖ 79 ተተኪ አመራር በተጨማሪ ስልጠና ተሰጥቷል።
- ❖ አዳዲስ ለተተኩ ስራ አስፈፃሚ ጉባኤ አባላት የግንዛቤ ማስጨበጫስልጠና ተሰጥቷል።
- ❖ የማእከል አባላት እና ወረዳ ማእከላት አገልግሎት ዋና ክፍል ሀላፊዎች ጋር ሁለት ቀን የአካል ዉይይትና የምስክር መርሐ ግብር ተደርጓል።

፬ በቤተክርስቲያን ሁለንተናዊ እድገት እና መንፈሳዊ ት/ቤቶች በ**2018** ዓ.ም በ**6** ወር የተከናወኑ ተግባራት ሪፖርት

- ➢ በ177 አብነት ትምህርት ቤቶች ለሚገኙ 238 መምህራንና ለ2,001 ደቀ መዛሙርት ብር 9,140,776.00 ወጪ በማድረግ ወርኃዊ የድጎማ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

- ከተለያዩ ገዳማት ለተወጣጡ 200 መነኮሳት እና መነኮሳይያት በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙርያ ሥልጠና ተሰቷል፡፡
- በተዘጋጀ መስፈርት መሠረት ከተለያዩ አብነት ትምህርት ቤቶች ለተውጣጡ የአብነት መምህራን በመምረጥ ብር 239,274.00 ወጪ በማድረግ ሥልጠና ተሰጥቷል፤
- ከተለያዩ አብነት ት/ቤቶች ለተውጣጡ ደቀ መዛሙርት ብር 233,677.00 ወጪ በማድረግ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ለአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ነጻ ትምህርት ዕድል ተጠቃሚዎችን የሥልጠናና ምክክር መርሐ ግብር በማዘጋጀት ማብቃትና ተልእኮ የተሰጠ ሲሆን ብር 234,420.00 ወጪ ተደርጓል፡፡
- የካህናት እጥረት ካለባቸው አካባቢዎች 10 ዲያቆናትን በመምረጥ በአጭር ጊዜ ለተሻለ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በአዳሪ አብነት ትምሕርት ቤት የአብነት ትምህርት እና ሥልጠና ተሰጥቷል፤
- ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ ችግር ላጋጠማቸው ገዳማት እና አብነት ት/ቤቶች 1.2 ሚሊየን ብር አስቸኳይ ድጋፍ አድርጓል፡፡
- በአፋር ሀገረ ስብከት የአዋሽ አርባ ደብረ ሓራ ቅ/ሚካኤል ወአቡነ አረጋዊ ገዳም በገነባው የአቡነ ዮናስ መታሰቢያ አብነት ት/ቤት 20 ደቀ መዛሙርትን ለሁለት ዓመታት አስተምሮ ያስመረቀ ሲሆን ለዚህም 401,000.00 ብር ወጪ አድርጓል፡፡
- በአሶሳ ሀገረ ስብከት እየተሰራ የሚገኘው አምባ አራት ሐመረ ኖኅ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ገዳም አ/ት/ቤት ግንባታ ፕሮጀክት 93% የተከናወነ ሲሆን ለፕሮጀክቱ ግንባታ ብር 3,268,534.04 ወጪ ተደርጓል፡፡
- በከፋ ሀገረ ስብከት እየተሰራ የሚገኘው የቦንጋ አ/ት/ቤት ግንባታ ፕሮጀክት 75% የተከናወነ ሲሆን ለግንባታ ፕሮጀክቱ ብር 2,190,006.43 ወጪ ተደርጓል፡፡
- በጌዴኦ፣ ኮሬና ቡርጂ ሀገረ ስብከት የአ/ት/ቤት ግንባታ ፕሮጀክት 12% የተከናወነ ሲሆን ለፕሮጀክቱ ግንባታው ብር 1,607,376.62 ወጪ ተደርጓል፤
- የበደሌ የገቢ ማስገኛ ሁለገብ ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክት 32% የተተገበረ ሲሆን ለፕሮጀክቱ ግንባታው ብር 897,202.00 ወጪ ተደርጓል፡፡

**፳ አባላት አገልግሎት ማስተባበሪያ በተመለከተ በ6ወር የተከናወኑ አበይት ጉዳዮች**

- 20 ማእከላት የማጠናከሪያ፣ቅኝት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- የአባላት መንፈሳዊ ህይወት ማሳደጊያ ስራወች በ25 ማእከላት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡
- 1900 አዳዲስ አባላት በሁሉም ማእከላት ማፍራት ተችሏል፡፡
- 288 ደጋፊና ተግባሪ አባላትን ማፍራት ተችሏል፡፡

**፱ የህዝብ ግንኙነት እና ትብብር አገልግሎት በተመለከተ በ6 ወራት የተከናወኑ አበይት ጉዳዮች**

- ለተቋቋመዉ የባለሙያ ህብረት የመሪ እቅድ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በዋናዉ ማእከል ልዩ የቨርቹዋል የድህረ ግቢ ምሩቃንን ጉባኤ እንዲዘጋጅ አድርጓል፡፡
- የማህበረ ቅዱሳንን አገልግሎትና ተቋማዊ ለዉጥ የሚደግፉ 34 አጋር አካላትን በዋናዉ ማእከል ማፍራት ተችሏል፡፡
- ማእከላት ለሁሉም አባላት የማህበሩን ርእይ፣ተልእኮ፣እሴትና አላማዎችን ምርሀ ግብር በአመት 4 ጊዜ እንዲዘጋጅ ድጋፍ አድርጓል፡፡
- የማህበሩን እቅድ  አፈፃፀም ዘገባ እና የቤተ ክርስቲያንን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳይ ዘገባ ለጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤ አቅርቧል፡፡
- ያረፉ ብፁዓን ወቅዱሳን ፓትርያርኮችና ብፁዓን  ጳጳሳት የሚታሰቡበት ዝክረ አበዉ መርሐ ግብር አዘጋጅቷል፡፡
- መፅሔተ ተልእኮን በህትመት በማዘጋጀት አሰራጭቷል፡፡
- ከጠቅላይ ቤተ ክህነት እስከ ሀገረ ስብከከት የሰንበት ትምህርትቤትአንድነትመዋቅርበማጥናት የአቅም ግንባታ ስራ ሰርቷል  ፡፡
- የማእከላትንና ግቢ ግባኤያትን ስርጭት የሚያሳይ ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

ማጠቃለያ

ማኅበረ ቅዱሳን በ፳፻፲፭ ዓ.ም የመጀመሪያ ፮ ወራት ውስጥ በስልታዊ ዕቅዱ የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። በተለይም በስብከተ ወንጌል ተደራሽነት፣ በአዳዲስ አማንያን ጥምቀት፣ በግቢ ጉባኤያት እንቅስቃሴ እና በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ረገድ የሚበረታቱ ውጤቶች ተመዝግበዋል። በቀሪዎቹ ፮ ወራት ዝቅተኛ አፈጻጸም የታየባቸውን ዘርፎች ለማጠናከርና የታቀዱትን ሜጋ ፕሮጀክቶች ለማስፈጸም ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራ ሪፖርቱ ያመለክታል።

## 4. ማኅበረ ቅዱሳን በማእከላት

### በማኅበረ ቅዱሳን የሰቆጣ ማእከል አመሠራረት አጭር ታሪክ

ሃይማኖት እንደ አባቶቻችን ጥበብ እንደ ዘመናችን የሚለው አባባል ሃይማኖት ፈጣሪዋ አንድ አምላክ እንደሆነ ሁሉ እርሷም አንዲት የሆነች ተቀዳሚ ተከታይ የሌላት ሊኖራት እንደማይገባ ሆና የተሠራች መሆኗንና ጥበብ ግን ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት፣ አማኝን ለማጽናትና ለማጠናከር ጊዜን፣ ገንዘብን፣ ጉልበትን አቀናጅቶ ለመሥራት አንድ ዓለማና ግብ ያላቸውን ክርስቲያኖችን በማደራጀት በአገልግሎት ክፍተት በሚታይበት ለመሸፈን የሚደረግ የአሠራር ስልት(ጥበብ) ነው፡፡

እንደ ልጅነቱ የሚገባውን አስተዋፅኦ ለማድረግ፣ ተመሳሳይ ዕድሜ ያላቸው ወጣቶች ተሰባስበው የጀመሩት ነው፣ ነገር ግን የቤተ ክርስቲያኒቱን ዘርፈ ብዙ ፈተና በቀናዒነት ሲታገል፥ አባላቱ እየጨመሩ፣ አገልግሎቱ እየሰፋ በግቢ ጉባኤ የሚያፈራቸው ኦርቶዶክሳውያን በገጠር አብያተ ክርስቲያናት ያላቸው ተሳትፎና ከአባላቱ የሚገኘው ክፍያ ለገዳማትና ለአብነት ጉባኤዎች መጠናከር ያለው ሚና ሲታይ ከዚህ በበለጠ ማኅበሩ ቢሠራ ቤተ ክርስቲያን ይህን ውጥንቅጥ የበዛበት ዓለም ዋጅታ እንድ ትሻገር ያስችላታል በሚል የማኅበሩ አገልግሎት አስፈላጊነት ከፍ ወደ አለ መዋቅር እንዲሸጋገር አድርጎታል፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን ሰቆጣ ማእከል ከማኅበረ ቅዱሳን ማእከላት አንዱ እንደ መሆኑ ብዙ የአገልግሎት ክንውኖችና የራሱ ታሪክ አለው።

የሰቆጣ ማእከል በ1991 ዓ.ም በወረዳ ማእከልነት ደረጃ በይፋ ከመመሥረቱ አስቀድሞ፣ በአካባቢው የነበሩ አባላት ወርኃዊ መዋጮ በመሰብሰብና አዲስ አበባ ወደ ሚገኘው ዋናው ማእከል በመላክ የአባልነት ግዴታቸውን ይወጡ ነበር። አባላቱ በአገልግሎት ረገድም በአቅራቢያቸው በሚገኙ አድባራትና ገዳማት ሰንበት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በመሳተፍ መንፈሳዊ ግዴታቸውን ይወጡ እንደነበር ይታወሳል። በ1989 ዓ.ም የተመሠረተውን የማኅበረ ቅዱሳን ወልድያ ማእከልን በመመሥረት ረገድ ጉልህ ሚና የነበራቸው፤ በአሁኑ ወቅትም ከታላቁ የሕዳሴ ግድብ ጋር ተያይዞ ከግብፅ ጋር ባለው ውዝግብ ኢትዮጵያን በመወከል ሙያዊ ትንታኔና ሙግት ከሚሰጡት ምሁራን አንዱ የሆኑት ዲያቆን ዶክተር በለጠ፣ አንድ ወቅት ለሥራ ቅኝት ወደ ሰቆጣ በመጡበት አጋጣሚ የማእከሉን መሠረት ለመጣል ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ዘጠናዎቹ አጋማሽ በነበሩት ዓመታት፣ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ተመርቀው ወደ አካባቢው የመጡት የቤተ ክርስቲያን ልጆች፣ በአገልግሎት ትጉህ፣ በሃይማኖት ጽኑና የወቅቱ የቤተ ክርስቲያን ልጆች፣ በአገልግሎት ትጉህ፣ በሃይማኖት ጽኑና የወቅቱ የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ የገባቸው ነበሩ። እነዚህ አባላት በግቢ ጉባኤያት አማካኝነት በትክክለኛው የክርስትና ሕይወት ታንጸውና ተቀርጸው የወጡ በመሆናቸው፣ በትምህርት አሰጣጣቸውም ሆነ በሕይወት ምሳሌነታቸው ለየት ያሉና አስተማሪዎች ነበሩ። ምንም እንኳ እንዲህ ብሎ ደፍሮ መደምደም አዳጋች ቢሆንም፣ በአሁኑ ወቅት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቁጥር መብዛት በግቢ ጉባኤ አባላት የጥራት ደረጃ ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ መምጣቱ የሚስተዋል ጉዳይ ነው።

በእነዚህ ዓመታት በግቢ ጉባኤ አልፈውና በዕውቀት ተኮትኩተው የመጡት እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ልጆች፣ በሰቆጣ ከተማ በሚገኙ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ ኮርሶችን በመስጠት ረገድ ንቁ ተሳትፎ ነበራቸው። የመንግሥት ሥራ ጫና ሳይበግራቸው መንፈሳዊ አገልግሎቱን ከምድራዊው ሥራ ጋር አጣጥመው በመሥራት ያሳዩት ቁርጠኝነትና በአጠቃላይ የነበራቸው ሥሙር አገልግሎት፣ ከሰንበት ትምህርት ቤቶች አልፎ በሕዝበ ክርስቲያኑ ዘንድ ከፍተኛ ዕውቅናንና ተቀባይነትን እንዲያገኙ አስችሏቸዋል። ማኅበረ ቅዱሳን በሰቆጣ በወረዳ ደረጃ እንዲቋቋም መነሻ የሆነውም፣ በወቅቱ የነበሩት የእነዚህ ትጉህ አባላት መኖርና ያሳዩት ተጨባጭ መንፈሳዊ ፍሬ ነው።

የማኅበረ ቅዱሳን የሰቆጣ ወረዳ ማእከል በይፋ የተመሠረተው ከወልድያ ማእከል በመጡ ልኡካን አማካኝነት ነበር፡፡ በማእከሉ የምሥረታ ሥነ ሥርዓት ላይ በወቅቱ የዋግ ኽምራ ሀጉረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ የነበሩት መልአከ ገነት መኮነን ኃይሉ በመገኘት አባታዊ ምክርና መንፈሳዊ ትምህርት ሰጥተዋል፡፡ በመርሐ ግብሩ ላይ መልአከ ገነት መኮነን "ይህ ማእከል ለምን እንደ ወልድያ ራሱን ችሎ አይቋቋምም?" በማለት ለወልድያ ማእከል ልኡካን ያቀረቡት ጥያቄ በማእከሉ ታሪክ ውስጥ የማይረሳ ትልቅ ክስተት ነበር፡፡

በምሥረታው ወቅት የማእከሉ ጽሕፈት ቤት የነበረው፣ አሁን ሀጉረ ስብከቱ የገነባው ባለ አራት ፎቅ (G+4) ሕንጻ ከመሠራቱ በ ፊት፣ በሰቆጣ ወረዳ ቤተ ክህነት ቅጥር ግቢ በስተ ጀርባ በኩል በነበሩት ክፍሎች ውስጥ ነበር፡፡ ማእከሉ አሁን ያለበትን የራሱን አዳራሽና የሥራ ክፍሎች እስኪገነባ ድረስ በዚያች ጠባብ ክፍል ውስጥ ለ12 ዓመታት ያህል በታላቅ ትዕግሥትና መንፈሳዊ ቁር ጠኝነት አገልግሎቱን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

በማእከሉ ታሪክ ውስጥ በወረዳ ደረጃ በነበረበት ወቅት የነበሩት የመጀመሪያዎቹ አባላት ለየት ያለ መንፈሳዊ ጥንካሬ የነበራቸው ቢሆንም፣ የአንዲት እኅታችንን ስም መጥቀስ የሌሎች ወንድሞችን አበርክቶ የሚያሳንስ አይሆንም፡፡ ይህች እኅታችን ፍሬ ሕይወት አሰፌ ትባላለች፤ እርሷ ለማኅበሩ አባላት ልዩ እናት ነበረች፡፡ ቤቷ ለማኅበሩ አባላት ማረፊያ ከመሆኑም ባለፈ፣ እንደ ሁለተኛ ጽሕፈት ቤትና የመሰብሰቢያ ቦታ በማገልገሉ ሁለንተናዊ ሕይወቷን ለአገልግሎት የሰጠች ልዩ እኅት ነበረች፡፡ በማእከሉ የሚገኙት አንድ የእንጨት ሸልፍና ወንበሮችም ማእከሉ በተመሠረተበት ወቅት በራሷ ወጪ አሠርታ ያበረከተቻቸውና ዛሬም ድ ረስ የእርሷን ባለውለታነት የሚያስታውሱ ስጦታዎች ናቸው፡፡

ፍሬ ሕይወት አሰፌ በሄደችበት ሀገር ሁሉ የማኅበሩን አሻራ በማኖር የምትታወቅ የተጋች እኅት ናት፡፡ ከኢትዮጵያ አልፎ በአ ፍሪካ ቦትስዋና በሥራ ምክንያት በሄደችበት ወቅት፣ እዚያ የሚገኙ የቤተክርስቲያን ልጆችን በማሰባሰብ የግንኙነት ጣቢያ እንዲ መሠረት በማረግ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረጓ ይታወሳል፡፡ ይህ ጥረቷም በወቅቱ በማኅበረ ቅዱሳን ዋናው ማእከል አማካኝነት በዜና ተዘግቧል በአጠቃላይ እርሷ በማኅበሩ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በአባላቱ ሕይወት ውስጥም ትልቅ የታሪክ ባለውለታ ናት፡፡

የሰቆጣ ወረዳ ማእከል ከአራት ዓመታት አገልግሎት በኋላ በ1995 ዓ.ም ወደ "ንኡስ ማእከል" ደረጃ አደገ፡፡ በዚህም የመልአከ ገነት መኮነን ኃይሉ ጥያቄ ከዓመታት በኋላ ምላሽ አገኘ፡፡ በወቅቱ ከአዲስ አበባ ከመጡ የዋናው ማእከል ልኡካን ጋር በመሆን ልዩ ልዩ ሥልጠናዎች የተሰጡ ሲሆን፣ የንኡስ ማእከል መዋቅርና የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ወደ ሥራ ተገብቷል (በወቅቱ "ማእከል" የሚለው ስያሜ ሳይመጣ "ንኡስ ማእከል" ይባል እንደነበር ልብ ይሏል)፡፡

የሰቆጣ ንኡስ ማእከል በራሱ ሥር የወረዳ ማእከላትና የግንኙነት ጣቢያዎችን የማቋቋም ኃላፊነት ነበረበት፡፡ የአምደ ወርቅ ወረዳ ማእከል ከሰቆጣ ወረዳ ማእከል ጋር በተመሳሳይ ጊዜ ወይም ቀደም ብሎ ተመሥርቶ ሊሆን ቢችልም፣መጀመሪያ ተጠሪነቱ ለወልዲያ ማእከል ነበር፡፡ በኋላ ግን የሰቆጣ ንዑስ ማእከል ይህንኑ መዋቅር በመያዝ፣ በጽጽቃንና በሰቆጣ ከተማ የወረዳ ማእከላትን፣ በአስከተማ ደግሞ የግንኙነት ጣቢያን በማቋቋም በድምሩ በሦስት የወረዳ ማእከላትና በአንድ የግንኙነት ጣቢያ አማካኝነት ሰፊ የሆነ መንፈሳዊ አገልግሎቱን ለማከናወን በቅቷል፡፡

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ የማኅበረ ቅዱሳን የሰቆጣ ማእከል አባላት ማኅበሩ በወረዳ ደረጃ በይፋ ሳይዋቀርና ሳይመሠረት አ ስቀድመው አገልግሎታቸውን ጀምረው ነበር፡፡ አባላቱ ወርኃዊ መዋጮአቸውን ለዋናው ማእከል አዲስ አበባ በመላክ የአባልነት ግዴታቸውን ከመወጣታቸውም በላይ፣ በአቅራቢያቸው በሚገኙ አድባራት ሰንበት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በመሳተፍ መንፈሳ ዊ ተልእኳቸውን በትጋት ይፈጽሙ ነበር፡፡ በሂደት ማእከሉ ካከናወናቸውና በዋናነት ጎልተው ከሚታወቁት ተግባራት መካከል የታሪክ ማስታወሻ ይሆኑ ዘንድ የሚከተሉትን ነጥቦች መጥቀስ ይቻላል፡-

በአሁኑ ወቅት ማእከሉ የአገልግሎት አድማሱን በከፍተኛ ሁኔታ በማስፋፋት፣ በ7 የወረዳ ማእከላት አማካኝነት መንፈሳዊና ማ ኅበራዊ ተልእኮውን ለሕዝበ ክርስቲያኑ ተደራሽ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

***ማእከሉ ከተመሠረተ ጀምሮ ያከናወናቸው አንኳር ተግባራት***

*ማኅበረ ቅዱሳን የሰቆጣ ማእከል ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ፣ በዋናው ማእከል የሚነደፉ ዕቅዶችን ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም በርካታ መንፈሳዊ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ ከእነዚህም መካከል በዋናነት የሚጠቀሱት የሚከተሉት ናቸው፡-*

***1. ዐውደ ርእይ ማዘጋጀት***

*ማኅበረ ቅዱሳን ዐውደ ርእዮችን በማዘጋጀትና በማቅረብ ረገድ የሚታወቅበትን ወጥ አሠራር በመከተል፣ የሰቆጣ ማእከልም ከ ዋናው ማእከል የሚላኩለትን ሰነዶች መሠረት በማድረግ በተደጋጋሚ ዐውደ ርእዮችን አዘጋጅቶ አቅርቧል፡፡ ማእከሉ ከሚላኩለት ሰነዶች በተጨማሪ እንደ ሰቆጣና እንደ ዋግ ኽምራ አህጉረ ስብከት ተጨባጭ ሁኔታ መታየት የሚገባቸው ን የታሪክ ሰነዶች በማዘጋጀት ረገድ የሚደነቅ ተሳትፎ ነበረው፡፡*

*ለመጀመሪያ ጊዜ በ1992 ዓ.ም የሰቆጣ ወረዳ ማእከል ከሰንበት ትምህርት ቤት ጋር በመቀናጀት ያቀረበው ዐውደ ርእይ ትልቅ ስ ኬት ያመጣ ነበር፡፡ ይህ ዐውደ ርእይ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን፣ ንዋያተ ቅድሳትንና አገልግሎታቸውን፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክን እንዲሁም በዋግ ኽምራ አህጉረ ስብከት የሚገኙ ታሪካዊ ገዳማትና አድባራትን በሚገባ ያስተዋ ወቀ ነበር፡፡ በአጠቃላይ ለማኅበረ ካህናቱና ለሕዝበ ክርስቲያኑ አራት ያህል ዐውደ ርእዮች ቀርበዋል፡፡ በተለይም ከ2000 ዓ.ም እስከ 2001 ዓ.ም ለሚሊኒየም መሸጋገሪያ የቀረበው ዐውደ ርእይ፣ በሰው ኃይል አሳታፊነቱና በዝግጅቱ ጥራት ለየት ያለ ነበር፡፡ ለሳምንት ያህል በቆየው በዚህ ዐውደ ርእይ ላይ ከልዩ ልዩ ወረዳዎች የመጡ ምእመናን የተካፈሉ ሲሆን፣ የማእከሉ አባላት ያላ ቸው አቅም የታወቀበትና "ሰቆጤ" የሚባለው የዜማ አቋቋም ሥርዓት ጭምር የቀረበበት ነበር፡፡*

***2. ታላላቅ ጉባኤያትን ማዘጋጀት***

*ማእከሉ ታላላቅ መንፈሳዊ ጉባኤያትን በማዘጋጀት የሕዝበ ክርስቲያኑን መንፈሳዊ ዕውቀት ለማሳደግ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ይህ አገልግሎት መምህራንን ከአዲስ አበባ በማስመጣት የሚከናወን በመሆኑ ሰፊ ዝግጅትንና ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ ነው፡፡ ማእከሉ በየዓመቱ ሁለት ጊዜ እንዲህ ያሉ ጉባኤያትን ለማካሄድ በማቀድ፣ ልዩ ልዩ ፈተናዎችን ተቋቁሞ የከተማው ሕዝበ ቃለ እግዚአብሔር እንዲማር ሲያደርግ ቆይቷል፡፡*

*በዚህ ረገድ በ2008 ዓ.ም በዐቢይ ጾም ወቅት የተከናወነው ጉባኤ በታሪክ የሚታወስ ነው፡፡ከትምህርቱ በተጨማሪ ስለ "ተሐድሶ" መናፍቃን ሥር መሠረትና ዓላማ ጥልቅ ግንዛቤ የተሰጠበት ነበር፡፡ ይህን ዝግጅት ከሌሎች በበለጠ በማቀናጀት፣ በጀቱን በማመቻቸትና ከልኡካኑ ጋር በመነጋገር ትልቁን ሥራ ሲሠራ የነበረው ባለውለታ ሊቀ መዘምራን ቀሲስ ግርማ አዳነ ነበ ር፡፡ ልዑል እግዚአብሔር ነፍሱን ከወዳጆቹ ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያዕቆብ አጠገብ ያሳርፍልን፡፡*

*በአሁኑ ወቅት የሰቆጣ ሕዝበ ክርስቲያን በወለህ ባሉት የመጻሕፍት መምህራን አማካኝነት የትምህርተ ወንጌል ምግብን ዕለት ዕለት እየተመገቡ ይገኛሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ታላቅ ዕድል እንደ ማግኘት፣ ምእመናንም በዕውቀትም ሆነ በሕይወት ለውጥ በማምጣት "መልካሙን መሬት" ልንመስል ይገባል፡፡*

*3. የልማት እንቅስቃሴ*

*ማኅበረ ቅዱሳን የሰቆጣ ማእከል መንፈሳዊ አገልግሎቱን በስፋትና በጥራት ለማከናወን በጀት ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ፣ ንዋያ ተ ቅድሳትንና መጻሕፍትን በማሠራጨት ራስን በራስ የመደጎም ሥራን እየተሠራበት ይገኛል፡፡*

*ማእከሉ ራሱን በገቢ ለማጠናከር ባደረገው ጥረት በ1996 ዓ.ም ጥቅምት ወር ላይ አሁን ያለችውን የኮንቴይነር ሱቅ በመክፈት ሥራ ጀምሯል። ለዚህም መነሻ የሚሆን በጀትን ኢንጂነር ዳንኤል ሽፈራው ካደረጉት የገንዘብ ድጋፍና ከአባላቱ ከተሰበሰበ*

መዋጮ በማሰባሰብ መጻሕፍትን፣ ዘቢብንና ዕጣንን በመግዛት ወደ ንግድ እንቅስቃሴ ገብቷል። የሱቁ መገኛም በአሁኑ ወቅት ተ ገኝ ባዩ ሆቴል ከተገነባበት ሕንጻ አጠገብ ባሉት ሱቆች በኩል ነበር።

በአሁኑ ወቅት ግን ማእከሉ የተሻለ ቤት በመከራየት የልማት ሥራውን በስፋት እያከናወነ ይገኛል።

4. ገጠር ተኮር ስብከተ ወንጌል

ይህ አገልግሎት ማኅበሩ ገና በወረዳ ማእከልነት ሳይቋቋም በፊት፣ በ1980ዎቹ ማብቂያ ዓመታት ጀምሮ በአባላቱ ጥረት ሲከናወ ን የቆየ ነው። አባላቱ ራቅ ያሉ ወረዳዎች ድረስ በመሄድ ወንጌልን ያስተምሩ ነበር። በተለይም እንደ ቀሲስ ዶ/ ር አበበ ምንዳ የመሳሰሉ አባላት የገጠር መንገድ መደበኛ ሥራቸው እስኪመስል ድረስ በከፍተኛ መንፈሳዊ ጥንካሬ ቅዳሜና እ ሑድን በመመላለስ ያገለግሉ ነበር። ይህ ገጠር ተኮር ስብከተ ወንጌል ዛሬም ድረስ በጥንካሬው ቀጥሎ ይገኛል።

**5. የስብከተ ወንጌል አዳራሽና ጽሕፈት ቤት ግንባታ**

ማእከሉ በአሁኑ ወቅት የሚገለገልበትን አዳራሽና ሁለት ክፍሎች ያሉት ጽሕፈት ቤት ለመገንባት በወቅቱ እጅግ ከባድና አታካች የሆኑ ፈተናዎች ተከሥተው ነበር። ሆኖም ግን በእግዚአብሔር ቸርነትና የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ በገባቸው ቅን አባቶች ድጋፍ ግንባታው ሊሳካ ችሏል።

በወቅቱ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ነበሩ። በግንባታው ሂደትም የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ መልአከ ገነት መኮነን ኃይሉና ወንድማቸው የደብረ ገነት መድኃኔዓለም ደብር አስተዳዳሪ ሊቀ ስዩማን ይኄይስ ኃይሉ ታላቁን ፈተና የተጋፈጡ ነበሩ። እነዚህ አባቶች ለማኅበሩ አገልግሎት ከቤተ ክርስቲያኑ ይዞታ ላይ ቦታ በመስጠት ግንባታው እንዲከናወን የወሰኑበት ታ ሪካዊ ወቅት ለማእከሉ ዕድገት ትልቅ መሠረት የጣለና የማይዘነጋ ውለታ ነው።

ለዚህ ሕንጻ ግንባታ መሳካት ትልቁን የገንዘብና የጉልበት አስተዋፅኦ ያበረከቱት በቁጥር አነስተኛ ቢሆኑም፣ በመንፈሳዊ ዓላማቸ ው ግን እጅግ ቁርጠኛ የነበሩ በሰቆጣ የሚገኙ የማኅበሩ አባላት ናቸው። ከእነርሱም በተጨማሪ የጽጽታና የአምደ ወርቅ ወረዳ ማእከላት አባላትም የሕንጻውን ግንባታ ዳር ለማድረስ የበኩላቸውን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

የሕንጻው ግንባታ ሲታቀድ የማኅበሩ አንጋፋ አባል የነበረው ጋሻው ገዛኸኝ የሕንጻውን ዲዛይን (ንድፍ) ከነዋጋ ዝርዝሩ በማዘጋ ጀት ለሥራ አስፈጻሚው አቀረበ። በወቅቱ የቀረበው የዋጋ ግምት አዳራሹንና ባለ ሁለት ክፍል ጽሕፈት ቤቱን ለመገንባት 120,0 00 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ) ብር እንደሚያስፈልግ የሚገልጽ ቢሆንም፣ ሕንጻው ተሠርቶ ያለቀው ግን ከቀረበው ግምት ባነሰ ወጪ ነበር። ለዚህም ዋናው ምክንያት አባላቱ በገንዘብ ከመደገፍ ባለፈ፣ በግንባታው ሂደት ላይ ያሳዩት ከፍተኛ የጉልበት ተሳትፎ ነው ።

ከዚህ በተጨማሪ በወቅቱ የማእከሉ ሰብሳቢ የነበሩት አቶ ምሕረቱ ሞላ፣ በአካባቢው የሚገኙ ባለሀብቶችን በማስተባበር እንደ አሸዋና ድንጋይ ያሉ የግንባታ ግብዓቶች በነጻና በትብብር እንዲቀርቡ በማድረጋቸው ለወጪው መቀነስ ትልቅ እገዛ አድርገዋል።

በተለየ ሁኔታ የሚጠቀሰው ግን የጋሻው ገዛኸኝ ጥረት ነው። እርሱ እንደ አንድ ባለሙያ ግንባታውን በቅያስ (ንድፍ) መሠረት አሥነስቶ ከመከታተል ባለፈ፣ እንደ ተራ ወዛደር ከሠራተኞች ጋር አብሮ በመሥራት፣ ዕለታዊ ሠራተኞችን (ወዛደሮችን) ከተራ ቦታ በማምጣትና ክፍያቸውን በመፈጸም ግንባታው እስከሚጠናቀቅ ድረስ ሙሉ ጊዜውን በመስጠት ኃላፊነቱን ተወጥቷል። በ እውነት እንደ እርሱ ያለ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ራሱን የሰጠ አባል ማግኘት ብርቅ ነው ማለት ይቻላል። ማእከሉ ዛሬም ድ ረስ መንፈሳዊ አገልግሎቱን እያከናወነ የሚገኘው በዚያ ታሪካዊ ወቅትና በእነዚህ ቁርጠኛ አባላት ተጋድሎ በተገነባው አዳራሽና ጽሕፈት ቤት ውስጥ ነው።


TECNO
CAMON 18



### 6. ከአጽራረ ቤተ ክርስቲያን (ከመናፍቃን) ጋር የተደረገ መንፈሳዊ ተጋድሎ

እንደ ሰቆጣ ከተማ ተጨባጭ ሁኔታ፣ ከመሠረታዊው ኦርቶዶክሳዊ ትውፊትና እምነት አንጻር መናፍቃን ገዝፈው የሚታዩበት እንቅስቃሴ አላቸው ማለት ባይቻልም፣ ይህ ምቹ ሁኔታ ግን ማኅበሩና ሕዝበ ክርስቲያኑ ምን ያህል እየተጠቀሙበት ነው? የሚለው ጥያቄ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

መናፍቃን ሲባሉ በሁለት ጎራ ተከፍለው የሚንቀሳቀሱ ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ገና ከመጀመሪያው ሚናቸውን ለይተው የቤተ ክርስቲያንን ልጆች በመንጠቅ ላይ የተሰማሩ ሲሆኑ፤ ሁለተኛዎቹ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰርገው በመግባት ወይም እዚያው ያሉትን በማስካድ "ቤተ ክርስቲያንን እናድሳለን" በሚል ስውር ተልእኮ ወደ መናፍቅነት ኅብረት ለመውሰድ የሚጥሩ "ተሐድሶ" መናፍቃን ናቸው። ሰቆጣ ከተማ ከሁለቱም ጎራዎች ጋር በተለያየ ጊዜያት ትግል ስታደርግ ቆይታለች።

በ1984 ዓ.ም. በፕሮቴስታንት ድርጅቶች በኩል የመጣውን ርዳታ "አንቀበልም" በማለት ሕዝበ ክርስቲያኑ በሰልፍ የወጣበትና ርዳታው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ተራድኦ ኮሚሽን በኩል እንዲሰጥ የተደረገበት ወቅት ታሪካዊ ክስተት ነበር። ለዚህም ስኬት የሰንበት ትምህርት ቤት አባላት ትልቁን ድርሻ ተወጥተዋል።

በተለይ የ"ተሐድሶ" አስተሳሰብ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ የተደረገው ትግል በዋናነት የሚጠቀስ ነው። መናፍቃን እንደ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የኑፋቄ ስልታቸውንና ስማቸውን እየቀያየሩ መከሠት መገለጫቸው ነው። በውጭ ሆነው ምእመናንን ማታለል ስላልቻሉ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመግባት ስውር ሤራቸውን ማካሄድ ጀምረዋል። ይህ እንቅስቃሴያቸው በይበልጥ ጎልቶ የታየው በ1991 ዓ.ም. በቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ ይማሩ የነበሩና በምንፍቅናው ወጥመድ ተጠልፈው የነበሩ መነኮሳትን ማኅበረ ቅዱሳን በቪዲዮ ካጋለጠው መነሻ ጋር ተያይዞ ነው።

በተለይም ከ1990ዎቹ ማብቂያ እስከ 2005/2006 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ፣ ተሐድሶዎች በርካታ ማኅበራትን በማቋቋም፣ ስልታዊ ዕቅድና የጊዜ ሰሌዳ አውጥተው፣ ከውጭ ሀገር ከሚንቀሳቀሱ የመናፍቃን ድርጅቶች ጋር በጀት ተመድቦላቸው በቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ዘመቻ የከፈቱበት ወቅት ነበር።

በወቅቱ በእነዚህ በተደራጁ የመናፍቃን ማኅበራት ውስጥ ከሚገኙ 80 ያህል ሰዎች መካከል የሁለቱ ሀገራቸው ሰቆጣ መሆኑን የሚገልጽ መረጃ ደረሰን። ይህ ኑፋቄ ሥር ሳይሰድ በሀገረ ስብከቱ አማካኝነት ወዲያውኑ እንዲበተን ተደርጓል። ዋናው ተጠርጣሪና አስተባባሪ የነበረው ግለሰብ ዲቁና ተቀብሎ አካባቢውን ለቆ የሄደ ቢሆንም፣ ከላይ ከተጠቀሱት ግለሰቦች ጋር ግንኙነት የነበረውና በደብረ ገነት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ "ማኅበረ ሎዛ" በሚል ስም የሚሰበሰብ ማኅበር ተቋቁሞ ነበር።

መጀመሪያ በሁለት ሰዎች የተጀመረው ይህ ጥርጣሬ ወደ ሰባት ሰዎች አድጓል። ከሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት አባላት ጋር በመቀናጀት፣ መረጃዎችን በማጠናከርና በቅርብ በመከታተል ለሀገረ ስብከቱ ቀረበ። በዚህም መሠረት አንዱ ተወግዞ እንዲለይና ለምእመናንም እንዲታወቅ ተደረገ። ሌሎቹ ግን በንስሓ ተመልሰው

በምእመናን ፊት ቤተ ክርስቲያንን ይቅርታ ስለመጠየቃቸው የተረጋገጠ መረጃ ባይኖርም፣ አሁንም በቤተ ክርስቲያንና በዐውደ ምሕረት ላይ ይታያሉ፡፡ በተለየ ሁኔታ በቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን "ዲያቆናት ነን" የሚሉና አስቸግረው የነበሩ የተወሰኑ ግለሰቦች ወደ መናፍቃን ጎራ ሄደው ተወግዘው ቢለዩም፣ በኋላ ላይ ግን ይቅርታ ጠይቀው ተመልሰዋል፡፡

እንዲህ ያሉ የኑፋቄ አስተሳሰቦች አሁንም ሆነ ወደፊት ሊከሡቱ ስለሚችሉ፣ ምእመናን በወሬ ደረጃ መረጃዎችን ከማናፈስ ይልቅ የመረጃ ሰዎች መሆን ይገባቸዋል፡፡ ያለ በቂ መረጃ ጥርጣሬን መዝራት ተጠርጣሪዎቹ ራሳቸውን እንዲደብቁና ስልታቸውን እንዲቀይሩ ስለሚረዳቸው፣ በትዕግሥት መረጃን መሰብሰብ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን የሰዎች መሰናክል መሆናቸው ሲረጋገጥ፣ ፈጥኖ በማጋለጥ ሤራቸውን ማክሸፍ ለቤተ ክርስቲያን ደኅንነት ወሳኝ ተግባር ነው፡፡

ማእከሉ በአሁኑ ወቅት እያከናወናቸው ያሉ አንኳር ተግባራት

ማኅበረ ቅዱሳን የሰቆጣ ማእከል ከምሥረታው ጀምሮ ያለፉትን ዘመናት በጽናትና በትጋት አሳልፎ፣ በአሁኑ ወቅት የአገልግሎት አድማሱን በማስፋፋት በርካታ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል። ማእከሉ በአሁኑ ሰዓት በትኩረት እየሠራባቸው የሚገኙት ዋና ዋና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡-

**1. ለገዳማትና ለአብነት ትምህርት ቤቶች የሚደረግ ድጋፍ**

ማእከሉ የቤተ ክርስቲያን የዕውቀት ምንጭና የሥርዓት መገኛ የሆኑትን ገዳማትንና የአብነት ትምህርት ቤቶችን ለመደገፍ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመንደፍና ሀብት በማፈላለግ፣ አባቶች መነኮሳትና ደቀ መዛሙርት በመጠኑ እየተደጎሙ ትምህርታቸውንና አገልግሎታቸውን እንዲቀጥሉ ዘርፈ ብዙ ድጋፎችን እያደረገ ይገኛል።

**2. ስብከተ ወንጌልን ማስፋፋትና የዕቅበተ እምነት ሥራዎች**

የወንጌተል ብርሃን ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆን ማእከሉ ከወለህ ነቅዓ ሕይወት ጉባኤ ቤት ጋር በመተባበር ሰፊ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል። ከእነዚህም መካከል፡-

በየዓመቱ ተተኪ መምህራንን በማሰልጠን፣ ገጠር ተኮር ስብከተ ወንጌልንና የዕቅበተ እምነት አገልግሎትን በማጠናከር የአጽራረ ቤተ ክርስቲያንን እንቅስቃሴ ለመግታት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው።

በማረሚያ ቤቶችና በመቄዶንያ የአረጋውያን መርጃ ቅርንጫፍ ማእከል ውስጥ መደበኛ የትምህርተ ወንጌል አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

ከወለህ ነቅዓ ሕይወት ጉባኤ ጋር በመሆን፣ ለወጣቶች የታለመ "የዕቅበተ አእምሮ" ወርኃዊ መርሐ ግብር በማዘጋጀት፣ ወጣቱ በትክክለኛው የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ታንጾ እንዲያድግና ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲቀርብ በትኩረት እየተሠራ ነው።

3. የግቢ ጉባኤያት አገልግሎት

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ተማሪዎች በቆይታቸው እምነታቸውንና ሥርዓታቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ፣ ማእከሉ ከአምስት በላይ ግቢ ጉባኤያትን በማቋቋም በኮሌጆች የሚማሩ ተማሪዎችን በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የማስተማርና የማነጽ ሥራውን አጠናክሮ ቀጥሏል።

4. ሐዊረ ሕይወትና ማኅበራዊ ተራድኦ

ምእመናን የገዳማትን በረከት እንዲሳተፉና ታሪካቸውን እንዲያውቁ፣ በቅርበት በሚገኙ ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት ሐዊረ ሕይወት (መንፈሳዊ ጉዞ) በማዘጋጀት ልዩ ልዩ መርሐ ግብሮችን ማከናወን ተችሏል። በተጨማሪም፣ በቅርቡ በተከሠተው ጦርነት ምክንያት ችግር ለደረሰባቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ማእከሉ አስፈላጊውን ሰብአዊ ድጋፍ በማድረግ የቤተ ክርስቲያንን አጋዥነት በተግባር አሳይቷል።

5. መዝሙርና ኪነ ጥበብ

በመዝሙርና በኪነ ጥበብ ዘርፍ፣ ማእከሉ የአካባቢውን ቋንቋና ባሕል መሠረት በማድረግ ወንጌልን ተደራሽ ለማድረግ እየሠራ ነው። በዚህም መሠረት 60 መዝሙራት በአካባቢው ቋንቋ (በኽምጣኛ) ተዘጋጅተው፣ በዋናው ማእከል አማካኝነት ሙሉ የስቱዲዮ ቀረጻ ሥራቸው ተጠናቆ ለምእመናን ሊቀርቡ በሚችሉበት ደረጃ ላይ ይገኛሉ።









የማእከሉ ጠቅላላ ጉባኤ በከፊል



አባላቱንና ሰንበት ተማሪዎችን እንዲሁም በጎ ፈቃደኞችን በማስተባበር በየዓመቱ የደም ልገሳ መርሐ ግብር እያከናወነ ይገኛል፡፡

ወጣቶች ሆነው ሳለ የወጣትነት ጊዜያቸውን ለእግዚአብሔር በማስገዛት፣ በትዕግሥትና በጽናት ያጋጠሟቸውን ችግሮች በእግዚአብሔር ቸርነትና በቅዱሳን ጸሎት ይሻገሩ ነበር፡፡ ይልቁንም ደግሞ የአንዳንድ የማኅበሩ አገልግሎት በገባቸው ብፁዓን አባቶች ድጋፍ፣ እንዲሁም እንደ ጋሽ ግርማ፣ ጋሽ ታዬ አብርሃም ባሉ አንጋፋ ወንድሞችና በሌሎችም ጠንካራ አባቶች ምክር ችግሩን ማለፍና ማሸነፍ ችለዋል፡፡ አሁንም ቢሆን ብዙ ፈተናዎች ቢኖሩም፣ እግዚአብሔርን አስቀድሞ ኢጋዥ በማድረግና በመጸለይ ፈተናዎችን መሻገር እንደ ዋና መመሪያ (መርህ) ሆኖ ያገለግላል፡፡

***መጽሔት ተልእኮ፡-*** እርስዎ በማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት በቆዩበት ጊዜ የማኅበሩን አገልግሎትና አስተዋጽኦ ከሀገርና ከቤተ ክርስቲያን አንጻር እንዴት ያዩታል?

***ዲያቆን ደምስ፡-*** እኔ ባለኝ ቆይታ በተማርኩትም ሆነ በተረዳሁት መሠረት፣ የማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት ለሀገርም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን እጅግ የላቀ አስተዋጽኦና አበርክቶ አድርጓል።

በመጀመሪያ ደረጃ፣ ወጣቱ በሥነ ምግባር የታነጸና የተማረ የሰው ኃይል እንዲሆን በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚከናወነው የማስተማር ሂደት ተጠቃሽ ነው፡፡ ትውልዱ "በእግዚአብሔር የለሽ" (አቴይዝም) መርህ ምክንያት እጅግ ወደ ተሳሳተ መንገድ ይጓዝ በነበረበት ወቅት ማኅበሩ መመሥረቱ፣ የነበረውን የሐሳብ ውዥንብር ከመቅረፍ አንጻር ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ወጣቱ በሥነ ምግባርና በሃይማኖት ታንጾ ለሀገርና ለወገን የሚጠቅም እንዲሁም ለሀገሩ የሚቆረቆር ትውልድ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ማኅበሩ ትልቅ አበርክቶ ነበረው። በተጨማሪም ታላላቅ አባቶችን አጉልቶ በማውጣት፣ ታሪካቸውን አጥንቶ በመዘከርና ትውልዱ እንዲያውቃቸው በማድረግ ረገድ የሚሠራው ሥራ የሚደነቅ ነው።

ቤተ ክርስቲያናችን ያላትን ሁለንተናዊ ገጽታ ዓለም እንዲያውቀው በማድረግ ረገድም ማኅበሩ የላቀ ድርሻ አለው። በተለይም ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ መጽሔት፣ ጋዜጣና የመሳሰሉት የሚዲያ ውጤቶች ባልተስፋፉበት ወቅት የቤተ ክርስቲያን ድምፅ በመሆን እስከ አሁንም ድረስ ያለውን የ"ሐመር" መጽሔት በማዘጋጀት ትውልዱ ግንዛቤ እንዲያገኝ አድርጓል። በሌላ በኩል ደግሞ በሚያዘጋጃቸው መንፈሳዊ ጉባኤያት፣ በተለይም ቃለ እግዚአብሔር በማይደርስባቸው የገጠር አካባቢዎች ሐዋርያዊ አገልግሎትን በማከናወን ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። ከጠረፍ እስከ ጠረፍ ከዐሥራ አምስት እስከ ሃያ ቀናት የሚፈጁ የሐዋርያዊ ጉዞዎችን በማድረግ የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ፣ ትምህርተ ሃይማኖትንና ኦርቶዶክሳዊ መዝሙራትን በማስፋፋት ረገድ እጅግ የላቀ ድርሻ ተወጥቷል።

የወጣቱን የንባብ ባሕል ለማዳበርም ከገጠር እስከ ከተማ ቤተ መጻሕፍትን በመክፈት የማንበብ ልምድ እንዲዳብር አድርጓል። አውደ ርዕዮችን በማዘጋጀትም ምእመናን "የእኔ ድርሻ ምንድነው?" ብለው እንዲጠይቁና መንፈሳዊ ቅናትና ቁጭት እንዲያድርባቸው የሚያደርጉ ሥራዎችን ሠርቷል። በጥናትና ምርምር ዘርፍም የአባቶቻችንን ትውፊት ተከትሎ የቤተ ክርስቲያንን መረጃዎች፣ ሥነ ጽሑፍን፣ ሥነ ጥበብን፣ ኪነ ሕንፃንና የዐውደ ምሕረት ጉባኤያትን በማስተዋወቅ ረገድ ትልቅ ሥራ አከናውኗል።

በመዝሙር ረገድ የነበሩ ውዥንብሮችን በተመለከተ፣ በተለይም የተሐድሶ መናፍቃን እንቅስቃሴ ጎልቶ በመጣበት ወቅት፣ ለምእመናን ትክክለኛውን የቤተ ክርስቲያን መረጃ፣ ሥርዓትና ትውፊት በማቅረብ ረገድ ማኅበሩ ትልቅ ሚና ነበረው።

መዝሙርን መሠረት አድርገው የሚሰነዘሩ ጥቃቶችን በማሳወቅ፣ ምእመናን ትክክለኛውን የቤተ ክርስቲያን አዘማመር አውቀውና የቅዱስ ያሬድን ዜማ ተከትለው እንዲዘምሩ፣ ራሳቸውንም ከተሳሳተ አስተምህሮ እንዲጠብቁ አድርጓል። እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን የዜማ መሣሪያዎች፣ በተለይም በገና አገልግሎቱ ቀርቶ በነበረበት ወቅት ዳግም እንዲያንሰራራና በስፋት አገልግሎት እንዲሰጥ በማድረግ ረገድ ትልቅ አበርክቶ አድርጓል።

ማኅበሩ እስከ አሁንም ድረስ እያገለገለ የሚገኝ ሲሆን፣ ወደፊትም ቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ የመሪነት ሚናዋን እንድትወጣ አገልግሎቱን አጠናክሮ ይቀጥላል። ከብፁዓን አባቶች፣ ከሚመለከታቸው የቤተ ክርስቲያን አካላትና ከባለድርሻ አካላት ጋር በአንድነት በመሆንም ድርሻውን ለመወጣት በትጋት እየሠራ ይገኛል።

**መጽሔተ ተልእኮ፦** ማኅበረ ቅዱሳን ከሠራቸው ዘርፈ ብዙ ሥራዎች ምእመናን በደምብ ቢያውቁት ብለው የሚያስቡትን ይንገሩን!

**ዲያቆን ደምስ፦** ቤተ ክርስቲያን በገጠርም ሆነ በከተማ ያለች፣ በወርቅም ሆነ በጨፈቃ የተሠራች፣ እርሷ አንዲት ናት። ምእመናን የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ በትክክል አውቀውና ተረድተው የራሳቸው ሱታፌ እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ እየተከናወነ ያለውን ሥራ ቢረዱና ቢደግፉት መልካም ነው ብዬ አስባለሁ። ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ሥልጣኔ በፊት የነበረች መሆኗን አውቆ፣ ከዳር ሆኖ ከመተቸት ይልቅ መሃል ገብቶ የአገልግሎት ተሳታፊ በመሆንና ለሌሎችም በማሳወቅ ረገድ ትልቅ ኃላፊነት አለብን።

ይህንን አገልግሎት ከቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪዎች ጋር በጋራ በመሥራት፣ የቀደሙ የአባቶቻችንን ትጋትና አስተዋይነት ሳይለቁ መጓዝ ያስፈልጋል። ማኅበሩ እስከ አሁን ከሚሄድበት በተለየ መልኩ ስልታዊ ዕቅድ በመንደፍ፣ ሁሉንም አሳታፊ የሚያደርግ የአገልግሎት በር ከፍቶ እየሠራ ያለውን ተግባር ለትውልዱ በሚገባ ማስተዋወቅ ይገባል።

በተለይም በዘመናዊነት ስም ከሚመጣው የቤተ ክርስቲያን ባሕል ወራራ ይልቅ፣ ነባር የቤተ ክርስቲያናችን ትውፊቶችና የትምህርት አስተምህሮዎች እንዲሁም ቅርሶቻችን የሚጠበቁበትን መንገድ ምእመናን ቢገነዘቡት እመኛለሁ። ነገ ተተኪ ማግኘት የሚቻለው የአብነት ትምህርት ቤቶች ሲኖሩ ነውና፣ የአብነት ትምህርት ቤቶቻችን ቁጥራቸውንና ይዘታቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ እየተከናወነ ያለውን አገልግሎት አውቆ የዚያ ተሳታፊ መሆን ቢቻል ትልቅ ለውጥ ያመጣል።

በገዳማትና በየገጠሩ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ተጠብቀው እንዲቆዩ የሚደረገውን አገልግሎት በጥልቀት ተረድቶ ተሳታፊና ባለ ድርሻ መሆንም እጅግ አስፈላጊ ነው። በጥቅሉ፣ የማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎትን ከሩቅ ከመስማት ይልቅ ጠጋ ብሎ ማኅበሩ ማነው? የሚለውን በሚገባ ቢረዱና ቢገነዘቡት የዘወትር ምኞቴ ነው።

**መጽሔተ ተልእኮ፦** ከማኅበሩ ምሥረታ ጀምሮ ለበርካታ ዓመታት ይዞ የቆየው የዐርብ ጸሎት ላይ ሲሳተፉ ነበር ይህን እንዴት አገኙት? በዚህ የጸሎት መርሐ ግብር ላይ በመሳተፍዎ ምን አገኙ? ምንስ ተጠቀሙ? ለአዲሱስ ትውልድ ምን ይመክራሉ?

**ዲያቆን ደምስ፦** ማኅበሩ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ያስቀመጡትን ተልእኮ መሪ ቃል በማድረግ፣ በአገልግሎት ውስጥ የሚያጋጥሙ ውጣ ውረዶችንና ፈተናዎችን ሁሉ ለመወጣት የሚጠቀምበት ትልቁ ጥበብ የሥጋ ፍልስፍና ሳይሆን ጸሎት ነው፡፡ ይህ ጸሎት በሁሉም ማእከላት ላለፉት 34 ዓመታት ሳይቋረጥ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ዐርብ ዐርብ አገልጋዩ ይበልጥ ለአገልግሎት የሚሰማራበት ወቅት በመሆኑ፣ በጋራ ተሰብስቦ ሳምንቱ እንዴት እንደተጠናቀቀ በመገምገም፣ የቀጣዩንም አገልግሎት እግዚአብሔር እንዲመራውና ፈተናዎችን እንዲያሳልፈው በጸሎት ይጠይቃል፡፡

የቀደሙ ወንድሞቻችን ይህንን ሥርዓት ሲያስቀምጡ የተጠቀሙበት ምሥጢር አለ፡፡ በመሆኑም እኛም እንደ ማኅበር ብቻ ሳይሆን በግል ሕይወታችንም ብዙ ተጠቅመንበታል፡፡ ከማኅበር ጸሎትነቱም በዘለለ፣ በግል ሕይወታችን የሚገጥሙንን ብዙ ፈተናዎች እንድንወጣና በጽናት እንድናገለግል ያደረገን ይህ ጸሎት ነው፡፡ ሁላችንም በፍቅር የምንወደውና የማናቋርጠው፣ ሥራችንን ለእግዚአብሔር ሰጥተን በሥጋ ጥበብ እንዳንፈላሰፍ የሚያደርገን በመሆኑ እስካለን ድረስ የምንሳተፍበት ነው፡፡

ለእኔ በግሌ የጸሎቱ ጥቅም ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይም በ2000 ዓ.ም አካባቢ በጤና ምክንያት ከባድ ሕመም ውስጥ ገብቼ ነበር፡፡ በወቅቱ ቆሞ መጸለይ ቀርቶ መራመድ እንኳ በማልችልበት ሰዓት፣ እዚሁ በአርብ ጸሎት በሚሳተፉ እኅቶቼና ወንድሞቼ ጸሎት አማካኝነት ከሕመሜ ድኛለሁ፡፡ ስለዚህ መቆም እስከቻልኩ ድረስ ከዚህ በረከት እንዳልለይ ለራሴ ቃል ገብቻለሁ፡፡ እግዚአብሔር በረዳኝ መጠን ከዚህ ጸሎት መለየት የለብኝም ብዬ ለመገኘት እሞክራለሁ፤ ለጥያቄዎቼ መልስ አግኝቼበታለሁ፡፡

መጪው ትውልድና ወጣቱም ቢሆን ይህንን ጸሎት እንደ ትርፍ ነገር ማየት የለበትም፡፡ ምክንያቱም ትልቁን ሥራችንን የሚያከናውነው ጸሎት ነው፡፡ ጸሎት የሁሉ ነገር መሣሪያና ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት ቋንቋችን ነው፡፡ አገልግሎታችን ውጤታማ የሚሆነው በጸሎት ኃይል ነው፡፡ በእውቀት ብንራቀቅም እግዚአብሔር ከሌለበት ከንቱ ነውና በጸሎት መበርታት እንዳለብን ከቀደሙ ወንድሞቼ ተምሬአለሁ፤ ስለዚህ ሁላችሁም ተጠቀሙበት ብዬ እመክራለሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በወሩ መጨረሻ እሑድ የሚካሄድ ወርኃዊ የትምህርት ጉባኤ አለ፡፡ ይህም ብዙ ቁም ነገር የምናገኝበት፣ የገጠሪቱን ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የምንረዳበትና መንፈሳዊ ሕይወታችንን የምንመረምርበት ጉባኤ ነው፡፡ ከሌሎች ሥራዎች አርፈን ነፍሳችንን በቃለ እግዚአብሔር የምናንጽበት ስለሆነ ምእመናን ተገኝተው እንዲማሩ ማመልከት እፈልጋለሁ፡፡ የቀደመውን አገልግሎት በማሰብና ቀጣዩም እንዲሳካ ይህንን ጉባኤ ቢሳተፉ መልካም ነው፡፡

በተጨማሪም በየዓመቱ በዐቢይ ጾም መጨረሻ ሳምንት (ከሆሳዕና በፊት ባለው ዐርብ) ሁሉም ማእከላት የሚሳተፉበት "ጸሎተ አኰቴት" የተሰኘ የምስጋና መርሐ ግብር አለ፡፡ ይህም እስከ አሁን የረዳንንና የጠበቀንን አምላካችንን የምናመሰግንበት፣ በአገልግሎት ደክመው አሁን ያረፉ አባቶችን፣ እናቶችንና ወንድም እኅቶችን የምንዘክርበት ነው፡፡ በደላችንን ሳይቆጥር በሰላም ዓመቱን ስላስጨረሰን በሁሉም ማእከላት የምናመሰግንበት መርሐ ግብር በመሆኑ፣ ምእመናን ከዚያም ላይ ቢሳተፉ የሚል መልእክት አስተላልፋለሁ፡፡

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** የማኅበረ ቅዱሳንን አገልግሎት አሁንም ወደፊትም ምእመናን በምን መልኩ መደገፍ ይችላሉ ብለው ያስባሉ?

**ዲያቆን ደምስ፡-** የማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት ዓላማ ለራሱ ዕውቅና ለመስጠት ሳይሆን፣ ቤተ ክርስቲያንን የተሻለ ደረጃ ላይ አድርሶ ይበልጥ ውጤታማ አገልግሎት እንድትሰጥና ማዕከላዊ የሆነ ጠንካራ የአገልግሎት ሥርዓት ሰፍኖ ለማየት በሚቻለው ሁሉ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት ነው፡፡ ማኅበሩ እያንዳንዱ ሰው ባለው ሙያ፣ አቅምና ተሰጥኦ ለቤተ ክርስቲያን እንዴት መሥራት እንዳለበት የሚያውቅባቸውን መንገዶች የሚያመቻች የአገልጋዮች ስብስብ ነው፡፡ በመሆኑም "ቤተ ክርስቲያንን እወዳለሁ፣ እደግፋለሁ" የሚል ማንኛውም ምእመን የሚሳተፍባቸው በርካታ የአገልግሎት በሮች ተከፍተዋል፡፡

ምእመናን በሚችሉት ሁሉ ባለፉበት አጥቢያ፣ በሰበካ ጉባኤ፣ በሰንበት ትምህርት ቤት እንዲሁም በልማቱ ዘርፍ በተለያዩ መንገዶች ማገልገል ይቻላሉ፡፡ ማንኛውም ምእመን "ምን ልሥራ? እንዴትስ ላገልግል?" ቢል፣ የአገልግሎት በሮች ተለይተው የተቀመጡና የተመቻቹ ሁኔታዎች ስላሉ፣ በዚያ ተሳትፎ ለቤተ ክርስቲያን የሚገባውን አስተዋጽኦ ማበርከት ይቻላል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ገና ያልተደፈኑ ብዙ ክፍተቶች ስሏሏት፣ ሁሉም ምእመን በሚችለው አቅም ቤተ ክርስቲያኑን መጠበቅና አንድ ነገር ማበርከት ይኖርበታል፡፡

እስከ አሁን በነበረው ጉዞ ማኅበረ ቅዱሳን በርካታ ሥራዎችን ሊያከናውን የቻለው አጋዥ ደጋፊ አባላትን፣ ቅንና ለጋሽ የቤተ ክርስቲያን ልጆችን በማስተባበር ነው፡፡ ስለዚህ አሁንም ማንኛውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባል ለሆኑ ሁሉ "ኑ አብረን በጋራ እንሥራ፣ ለውጥም እናመጣለን" በማለት ጥሪውን ያቀርባል፡፡ማኅበሩ አዲስ ስልታዊ ዕቅድ ሲነድፍ ባለ ባለድርሻ አካላትን ለማሳተፍ በርካታ የአገልግሎት በሮችን አዘጋጅቶ በቁርጠኝነት ተነሥቷል፡፡

በመሆኑም ወደ ማኅበሩ አገልግሎት በመቅረብ፣ በአቅራቢያችሁ በሚገኙ ማእከላትም ሆነ በአምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ወደሚገኘው የማኅበሩ ዋና ጽሕፈት ቤት በመምጣት መሳተፍ ይቻላል፡፡ በሐሳብ፣ በጸሎት፣ በማቴሪያልና በገንዘብ መደገፍ የሚቻልባቸው መንገዶች ስላሉ "ኑ በጋራ በመሥራት የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት አብረን እናከናውን" እንላ ለን፡፡

**መጽሔተ ተልእኮ፦** በመጨረሻም መጨመር የሚፈልጉት ሐሳብ ወይም ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልእክት ካለዎት?

**ዲያቆን ደምስ፦** ይህ አገልግሎት ሁሉንም የሚያሳትፍና እያንዳንዱ ምእመን ባለቤት የሚሆንበት ነው፡፡ በተለይ በዚህ ወቅት ማኅበረ ቅዱሳን ለብዙ ነገሮች ተጠያቂ የሚሆንበትና "ምን ሠራ?" ተብሎ የሚጠየቅበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን ማለት የሁላችን ስብስብ ሲሆን፤ ለቤተ ክርስቲያን አንድነት፣ ለአገልግሎት መስፋፋትና ለዕድገቷ መፋጠን የሚተጋ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ቀድሞ የነበራትን መሪነትና ግንባር ቀደምትነት ጠብቃ እንድትቀጥል፣ አባቶቻችንን በጸሎት እየደገፍንና የሚሉትን በመታዘዝ የምናገለግልበት ማኅበር ነው፡፡

ማኅበሩ ገና ያልደረሰባቸውን ጠረፋማ የገጠር ቦታዎች በጥሩ እንቅስቃሴ ለማገልገልና እየመጡ ያሉትን ፈተናዎች በሙሉ በጋራ ለማለፍ አንድነታችንና ኅብረታችን እጅግ ያስፈልጋል፡፡ ያስፈልጋል፡፡ ከውጭ ሆኖ ከመተቻቸትና ጣት ከመጠቋቆም ይልቅ፣ ሁላችንም በአንድነት ብንቆም መሰባሰባችን ለቤተ ክርስቲያን ኃይልና ጉልበት፣ ለአባቶቻችን አቅም፣ ለሚሠሩ ሰዎችም ትልቅ ድጋፍ ነው፡፡ በመሆኑም ሁላችንም አንድ እንሁን፡፡

በተለይ ደግሞ "ትንሿ ቤተ ክርስቲያን" በምትባለው በቤተሰባችን ውስጥ ልጆቻችንን በጥሩ ሥነ ምግባር አንጾ ለማሳደግ፣ የአቡነ ጎርጎርዮስ ትምህርት ቤት ሕፃናትን ቀርጾ በማሳደግ ረገድ ትልቅ ሥራ እየሠራ ስለሚገኝ ልጆቻችንን በዚያ መንገድ ብናስተምርና ብናሳድግ መልካም ነው እላለሁ፡፡ ሁላችንም ወደ ማኅበሩ በመምጣት የበኩላችንን እንወጣ፤ ብዙ የአገልግሎት በሮች ስላሉ "ጋን በጠጠር ይደገፋል" እንዲሉ፣ ሁላችንም ብንደጋገፍና ብንተባበር መልእክቴ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይስጥልኝ፡፡

**መጽሔተ ተልእኮ፦** እግዚአብሔር ይስጥልን ቃለ ሕይወት ያሰማልን መምህር!

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር!**

## 6. ይናገራልፎቶው



ከኮንታና አካባቢው በመምጣት ቃሊቲ ቅዱስ ገብርኤል ሰንበት ት/ቤት የሠለጠኑ ሠልጣኞች



ቤንቺ ማጂና አካባቢው በመምጣት አቡነ አረጋዊ ወገብረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት የሠለጠኑ ሠልጣኞች



ከወላይታና አካባቢው በመምጣት ጀሞ መድኃኔዓለም ሰንበት ት/ቤት የሠለጠኑ ሠልጣኞች




የአባላትን አቅም ለማሳደግ የአባላት ማትጊያ መርሐ ግብራት የማካሄድ ሥራ እየተሠራ ነው፡፡



በማእከሉና በሁለት ወረዳ ማእከላት የዜማ መሣሪያ(የበገና) ሥልጠና እየሰተጠ ይገኛል፡፡

**ማእከሉ በአሁኑ ወቅት የሚጋፈጣቸው ዋና ዋና ተግዳሮቶች**

ማኅበረ ቅዱሳን የሰቆጣ ማእከል በታሪክ ሂደቱ በርካታ ድሎችን ያስመዘገበ ቢሆንም፣ በአሁኑ ወቅት የአገልግሎቱን ቀጣይነት የሚፈትኑ ጥቂት የማይባሉ ተግዳሮቶች ተደቅነውበታል፡፡ እነዚህም ተግዳሮቶች በማእከሉ የሥራ አፈጻጸም ላይ የራሳቸውን አሉታዊ ተጽዕኖ አሳርፈዋል፡፡

**1. ከፍተኛ የአባላት ፍልሰትና የተተኪ አገልጋይ እጥረት**

የሰቆጣ ማእከል አባላት ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑት ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በሥራ ምክንያት ወደ ሰቆጣ የመጡ ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህ አባላት የሥራ ጊዜያቸውን አጠናቅቀው ወይም የሥራ ዝውውር አግኝተው ወደ መጡበትና ወደ ሌሎች አካባቢዎች ሲሄዱ፣ ማእከሉ በየጊዜው ከፍተኛ የሆነ የአባላት ፍልሰት ያስተናግዳል፡፡ ይህ ሁኔታ በተረጋጋ ሁኔታ አገልግሎቱን የሚመሩና ኃላፊነትን የሚረከቡ ተተኪ አገልጋዮችን ለማግኘት ማእከሉን ትልቅ ፈተና ውስጥ ጥሎታል፡፡

**2. የአባላት በመንፈሳዊ ሕያወት አለመጠንከር**

በአሁኑ ወቅት ቤተ ክርስቲያናችን በመዋቅር ደረጃ እየተፈተነች ባለችበት፣ የክርስቲያኖች እልቂትና የአድባራትና ገዳማት መቃጠል ዕረፍት በነሳበት በዚህ አስቸጋሪ ወቅት፣ ጠላት ስልታዊ በሆነ መንገድ ጥቃቱን እያፋጠነ ይገኛል፡፡ ሆኖም ግን፣ ይህንን ታላቅ የቤተ ክርስቲያን መከራ ተገንዝቦ በንቃት ከመሥራት ይልቅ፣ በአብዛኛው የወረዳ ማእከላት በሚገኙ አባላት ላይ ድካም ይታያል፡፡

ከዜና ቤተ ክርስቲያን የራቀና ስለ እናት ቤተ ክርስቲያን መከራ ቢሰማም ምንም የማይሰማው ሆኖ መገኘት ለማእከሉ ትልቁ ፈተና ሆኖበታል፡፡ የማእከሉን መንፈሳዊ ዕድገት የሚያቀጭጨው የአባላት ቁጥር ማነስ ብቻ ሳይሆን፣ ያሉትም ቢሆኑ መንፈሳዊ ትጋታቸው መላላቱና ለቤተ ክርስቲያን ጥሪ የሚሰጡት ምላሽ ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡

**3. የገንዘብና የኢኮኖሚ አቅም ማነስ**

ለማእከሉ መንፈሳዊ አገልግሎትና ለተለያዩ የልማት ሥራዎች ማስፈጸሚያ የሚሆን በጀት ማግኘት ሌላኛው ፈታኝ ጉዳይ ነው፡፡ በማእከሉ የሚገኙት አባላት ቁጥር ውስን መሆንና ማእከሉን በገቢ የሚደግፉ ቋሚ የልማት ተቋማት አለመኖራቸው፣ የአገልግሎት አድማሱን ለማስፋት በሚደረገው ጥረት ላይ እንቅፋት ፈጥሯል፡፡

በዚህ ረገድ በ1990ዎቹ አካባ የነበሩ አንጋፋ አባላት በወቅቱ የነበረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም ለማእከሉ ቋሚ የገቢ ምንጭ የሚሆኑ የልማት መሠረቶችን ባለመጣላቸው፣ ዛሬ ላይ ከፍተኛ ቁጭት ፈጥሯል፡፡ ማእከሉ የራሱ የሆነ ቋሚ ይዞታና የገቢ ምንጭ ቀደም ብሎ አለመያዙ፣ የዛሬው ትውልድ በትልቅ የፋይናንስ ችግር ውስጥ እንዲወድቅ ምክንያት ሆኗል፡፡

ማእከሉ በአሁኑ ጊዜ ከላይ በተጠቀሱት ዝርዝር ሁኔታዎችና በሌሎች በማንኛውም የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ለማሳለጥ በሚጠቅሙ መንገዶች ምእመናንና ምእመናት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡና አገልግሎቱን እንዲደግፉ ይሻል።



## 5. ቤተ አናግድ

ሰላም ውድ አንባብያን! እንደምን ሰነበታችሁ! የአምላካችን የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን! የዛሬ እንግዳችን ዲያቆን ደምስ ይባላሉ። ዲያቆን ደምስ የማኅበረ ቅዱሳን አንጋፋና መጀመሪያዎቹ አገልጋዮች ከሚባሉት መካከል አንዱ ሲሆኑ ከመነሻው ጀምሮ እስካሁን ያለውን የማኅበሩን አገልግሎት ሂደትና የግል ተሞክሮአቸውን እንዲያካፍሉን በጋበዝና ቸው መሠረት የቤተ አናግድ ዓምድ እንግዳችን አድርገናቸዋል፤ ትከታተሉን ዘንድ በአክብሮት እንጋብዛችኋለን!

***መጽሔት ተልእኮ፡-*** *ዲያቆን ደምስ በቅድሚያ ከልጅነትዎ ጀምሮ እስካሁን ያለዎትን የአገልግሎት ተሞክሮ ለእኛ ለማካፈል እንግዳችን ሁነው ስለተገኙ እናመሰግናለን በመቀጠልም የልጅነት ሕይወትና በመጀመሪያ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለአገልግሎት የመጡበት መንገድስ ምን ይመስል ነበር?*

***ዲያቆን ደምስ፡-***

የተወለድኩት እዚሁ አዲስ አበባ፣ ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ነው። ይሁን እንጂ ክርስትና ከተነሣሁ በኋላ በቤተሰቦቼ የሥራ ዝውውር ምክንያት ወደ ሰላሌ ፊቼ በመሄዴ በዚያው ለማደግ ችያለሁ። ዕድሜዬ ለትምህርት ሲደርስ ቅዱስ ጊዮርጊስ በሚባለው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በዚያን ጊዜ "የቄስ ትምህርት ቤት" ተብሎ ወደሚጠራውና ሕፃናት የአብነት ትምህርት ወደሚቀስሙበት ቦታ ገብቼ መማር ጀመርኩ። በዚያም ማንኛውም ተማሪ ትምህርት ሲጀምር የሚማራቸውን

የንባብ ሥርዓት፣ አቡጊዳንና መልእክተ ዮሐንስን ተማርኩ። እነዚህን ሳጠናቅቅ ዳዊትና ውዳሴ ማርያም በመማር ላይ ሳለሁ በሕመም ምክንያት ትምህርቴን አቋረጥኩ፤ ከሕመሜ ካገገምኩ በኋላም በቀጥታ ወደ ዘመናዊው (የአስኳላ) ትምህርት ገባሁ። ነገር ግን በተለይ ዐሥራ አንደኛ ክፍል እያለሁና ከዚያም በኋላ በነበረኝ የዩኒቨርሲቲ ቆይታ የአብነት ትምህርቱን በተወሰነ መልኩ ለማስቀጠል ችያለሁ።

የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን እዚያው ሰላሌ ፊቼ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ከአንደኛ እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ተምሬ አጠናቀቅኩ። በተለይም በ1985 ዓ.ም አካባቢ፣ ከብላቴ መልስ የማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት በጣም ተስፋፍቶ በነበረበት ወቅት፣ በፊቼ ደብረ ሰላም ላይ ከሁሉም የተሻለ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ነበረ። በዚያም ወቅት በረከታቸው ይድረሰኝና አባ ወርቅነህ ውቤ መጽሐፍ ቅዱስን ሁልጊዜ ያስተምሩ ነበር። እርሳቸው አንድም ተማሪ ቢሆን እንኳ ይዘው የሚያስተምሩበት ትጋት ስለነበራቸው፣ እኛም በእርሳቸው ዘንድ ተሰባስበን መማር ጀመርን።

መጽሐፍ ቅዱስን ዘርግተው እያስተማሩን በነበረበት በዚያ ወቅት፣ መምህር ብርሃኑ አያሌው የሚባለው ወንድማችን ከአዲስ አበባ ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ ተመርቆ ወደ ፊቼ መጣ። መምህር ብርሃኑ ሲመረቅ የማኅበሩን አገልግሎት እንዲያስፋፋ አደራ ተሰጥቶት ስለነበር፣ እዚያው ተገናኝተን ስለ ማኅበረ ቅዱሳን መነጋገር ጀመርን። እርሱም የተሰጠውን አደራ ለመወጣትና የማኅበሩን እንቅስቃሴ ለማስቀጠል ጥረት ያደርግ ስለነበር፣ በዚያ መሠረት የማኅበረ ቅዱሳን የፊቼ ማእከልን ለመመሥረት እንቅስቃሴ ተጀመረ፤ እኔም በዚያ ሂደት ውስጥ አብሬ ነበርኩ።

ከዚያም በኋላ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መጣሁ። የገባሁትም ወደ ስድስት ኪሎ ግቢ ሲሆን፣ በዚያም የግቢ ጉባኤ እንቅስቃሴ በስፋት የሚሠራበት ስለነበር ከወንድሞችና ከእኅቶች ጋር በመገናኘት አገልግሎት ጀመርኩ። ልክ በ1986 ዓ.ም ስድስት ኪሎ ግቢ ጉባኤ የመዝሙር ክፍል ተወካይ በመሆን ወደ ማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት የመምጣት አጋጣሚውን አገኘሁ። በወቅቱ ከሌሎች ሁለት ወንድምና እኅቴ ጋር በመሆን ግቢ ጉባኤያችንን በመወከል ወደ ማእከል እየመጣን መዝሙር እናጠናም እናስጠናም ነበር።

በ1987 ዓ.ም የማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት ከነበረው በበለጠ ሁኔታ በመስፋፋቱ፣ በጽሕፈት ቤት ያገለግል የነበረው ወንድማችን ግርማ ወልደ ሩፋኤል በሥራ ምክንያት ወደ ባሌ ጎባ ሲሄድ፣ ያንን ቦታ እኔ እንድይዝ ተደረገ። ከዚህ ጊዜ በኋላም ወደ መደበኛ አገልጋይነት መጣሁ። በአሁኑ ወቅት ባለትዳር ስሆን፣ የአንድ ሴት ልጅና የአንድ ወንድ ልጅ አባት ነኝ።

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** የአስኳላ ትምህርትና የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትን በልጅነት ወቅት እንዴት አጣጣሙት?

**ዲያቆን ደምስ፡-** በልጅነት ዕድሜዬ ከቤተሰቦቼ ጋር በመሆኔና በዚያን ወቅት የሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎት በስፋት ተጠናክሮ ባለመኖሩ፣ በሰንበተ ክርስቲያን ተገኝቶ ከማስቀደስና በበዓለ ጥምቀት ታቦት አጅቦ ከመውጣት ውጪ በጣም ጠለቅ ያለ አገልግሎት አልነበረም፡፡ ከ1985 ዓ.ም በኋላ ግን የሰንበት ትምህርት ቤቶች እየተጠናከሩ ሲመጡ፣ እኔም በፍቼ ደብረ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል ሰንበት ትምህርት ቤት በትጋት መሳተፍ ጀመርኩ፡፡

በመቀጠልም ወደ ዩኒቨርሲቲ ስገባ የማኅበረ ቅዱሳን የግቢ ጉባኤ አገልግሎት በስፋት ተጠናክሮ ስለነበር በዚያ ላይ እየተሳተፍኩ አገለግል ነበር፡፡ በተለይ በስድስት ኪሎ ግቢ በነበርኩበት ወቅት፣ ገና ወጣት ብሆንም ከሰዎች ጋር ቶሎ የመግባባት ተሰጥኦ ስለነበረኝ በትክክለኛው መንገድ በጥልቀት አውቄ መገልገልና ማገልገል የጀመርኩት በዚህ ጊዜ ነው፡፡ ያን ጊዜ በተለይ በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን "የነዳያን ጉባኤ" በሚል ሠራተኛ ተቋቁሞ ሰዎችን እያስተማርን ለሥጋ ወደሙ እንዲበቁ ማድረግ የቻልንበት ወቅት ነበር፡፡ ያኔ ሥጋ ወደሙ የተቀበሉና አሁን ድረስ በጽናት የቆዩ አባቶች፣ እናቶች፣ ወንድሞችና እኅቶች ሲያገኙን በትልቅ አክብሮትና ሰላምታ ያናግሩናል፡፡

እግዚአብሔር ይመስገንና አገልግሎቱ የአስኳላ ትምህርቴን ሳይበድለው፣ ትምህርቴም አገልግሎቱን ሳይበድለው ሁለቱንም ጎን ለጎን በማስኬድ በአስኳላው ትምህርቴ ሁለተኛ ዲግሪዬን መማር ችያለሁ፡፡

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** ወደ ማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት ኅብረት እንዴት ተቀላቀሉ? በመጀመሪያ ወቅት የነበረው የማኅበሩ አገልግሎት፣ የወንድማማች ኅብረቱና የነበረው ቤተሰባዊነት ምን ይመስል ነበር?

**ዲያቆን ደምስ፡-** ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት፣ ወደ ማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት የተቀላቀልኩት በግቢ ጉባኤ ተሳትፎዬ ሲሆን፣ በኋላም በመደበኛ አገልጋይነት ቀጥያለሁ። በተለይ በዚያ ወቅት የነበሩት ቀዳማውያን ወንድሞችና እኅቶች ፍጹም ትሕትና በተላበሰና በመንፈሳዊነት ስሜት ውስጥ ሆነው የሚያገለግሉበት መንገድ የሚደንቅ ነበር። በዚህ ሂደት ውስጥ ያለፈ ሰው ሁሉ በአገልግሎቱ ተመስጦ እዚያው እንዲቀር የሚያደርግ ድባብ ነበረው።

የወንድማማችነት ኅብረቱና ቤተሰባዊነቱ እጅግ የተለየ ነበር። በተለይ መደበኛ አገልጋይ በነበርኩበት ወቅት፣ የምንለብሰውን ልብስ እንኳ ሳይቀር የሚያለብሱን (ልብስ የሚሰጡን) ወንድሞች ነበሩ። ያ የወንድሞች ኅብረት እጅግ የሚደንቅ ነበር። አሁን ቆም ብዬ ሳስበው 'ይህን ሁሉ ለማድረግ ምን ይገፋፋቸው ነበር? በልባቸው ውስጥ የአገልግሎት ፍቅር እንዴት ቢሠርጽ ነው?' ያሰኛል። በውስጣቸው የነበረው ትጋትና ለቤተ ክርስቲያን የነበራቸው 'ቁጭት' እጅግ የሚያስደንቅ ነበር። ያንን ቀዳሚ ቁጭትና ትጋት ለአሁኑ ዘመን አገልጋዮች ቢያሳውቁልን የዘወትር ምኞቴ ነው።

ከየትኛውም ማእከል ለሚመጡ ወንድሞችና እኅቶች የነበራቸው ፍቅር ፍጹም ቤተሰባዊ ነበር። አብሮ የማደር፣ የናፍቆትና የጨዋታ ጊዜያችን ሁሉ ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቻ ነበር፤ እንቅልፍ የሚባለው ነገርም አይታሰብም ነበር። በተለይ በገጠሩ አካባቢ የሚከናወነውን አገልግሎት ከማእከል የሚሄዱ ወንድሞችና እኅቶች በታላቅ 'ቁጭት' ነበር የሚገልጹት። በዚያ ያለውን የሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎት ለማጠናከር፣ ንኡስ ማእከላትን ለመክፈትና አገልግሎቱን ለማስፋፋት ቀንና ሌሊት ይደክሙ ነበር። በዚህ ሂደት ውስጥ አብሬ በማገልገሌ ትልቅ ደስታ ይሰማኛል።

የነበራቸው የአገልግሎት ፍቅርና ተመስጦ ቤተሰብን እንኳ የሚያስረሳና በፍጹም የቤተ ክርስቲያን ፍቅር ውስጥ እንድኖር የሚያደርግ ነበር። ይህ ሁኔታ ከእነርሱ ጋር እንድኖር፣ አብሬ እንድገለገልና እንዳገለግልም አድርጎኛል። የአገልግሎቱ ቅናት አድሮብኝ በዚያው ተቀላቀልኩ፤ ከመደበኛ አገልጋይነት ብለቅም እንኳ እስካሁን በማኅበሩ አገልግሎት ውስጥ እገኛለሁ። እውነቱን ለመናገር፣ ለማኅበሩ አገልግሎት ባልጠቅምም እኔ ግን እስካሁን እየተጠቀምኩበት እገኛለሁ።

በዚያ ወቅት የነበሩት አገልጋዮች ለቤተ ክርስቲያን የነበራቸው ፍቅር ልዩ ነበር። ቀን በመደበኛ ሥራቸው ውለው፣ ማታ ማኅበሩ ባለው ትንሽ ክፍል ውስጥ ትልቅ ትንሽ ሳይሉ ሁሉንም በፍቅር እያሳተፉ ያገለግሉ ነበር። ብዙ ፈተናና ውጣ ውረድ ቢኖርባቸውም፣ ያንን መከራ እነርሱ እየተቋቋሙ እኛ ግን በአገልግሎት እንድንጸና፣ ማኅበሩን እንድንወድና በሕይወታቸው ክርስትናን በተግባር ይኖሩት ስለነበረ ለእኛም ትልቅ ጽናትና ትምህርት ሆነውናል።

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** ማኅበረ ቅዱሳን ሲመሠረት የነበሩ የማኅበሩ ወቅታዊ ፈተናዎች ምን ምን ነበሩ?

**ዲያቆን ደምስ፡-** ማኅበሩ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ፣ አንጋፋ ወንድሞችና እኅቶች እንደሚነግሩን፣ በተለያዩ ጊዜያት ከውስጥም ከውጭም የተለያዩ ፈተናዎች ይፈራረቁበት ነበር፡፡ በተለይም ወጣቱ በዚህ ደረጃ ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቀናዒ ሆኖ መነሣቱን ካለመረዳት የተነሣ፣ በአንዳንድ የቤተ ክህነት ሠራተኞች፣ በተለያዩ አድባራትና ገዳማት በሚገኙ አገልጋዮች፣ እንዲሁም "ሃይማኖተ አበው" በሚባለው ማኅበር ርዝራዦች በኩል ማኅበሩን ያልተረዱ አካላት ብዙ ፈተናዎችን ይጥሩ ነበር፡፡ በተጨማሪም የማኅበሩን አገልግሎት በሚገባ ያልተረዱ የመንግሥት አካላትም ጭምር የሚፈጥሯቸው የተለያዩ ፈተናዎች ነበሩ፡፡

እነዚያን ሁሉ ፈተናዎች ለማለፍ የሚጠቀሙበት ትልቁ መንገድ፣ አገልግሎቱን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አሳልፎ በመስጠት ነበር፡፡ እዚህ ላይ የብፁዕ አባታችን የአቡነ ጎርጎርዮስ ትምህርትና ምክር የወደፊቱን ታሳቢ ያደረገ እይታ እንዲኖራቸው በማድረጉ፣ አገልጋዮቹ ሌላ ነገር እንዳይመለከቱ ረድቷቸዋል ብዬ አስባለሁ፡፡ እስከ ዛሬም ድረስ ማኅበሩ በተለያዩ ጊዜያት የሚገጥሙትን ፈተናዎችና ዕንቅፋቶች የሚወጣበት መንገድ፣  ያኔMየተማሩበትንና የተረዱበትን መሠረት ያሳያል፡፡ በፍቅርና በቁርጠኝነት የሚያገለግሉ በመሆናቸው፣ በጭራሽ የሰው ትምክህት አልነበራቸውም፤ በባለሥልጣናትም ሆነ በማንኛውም ምድራዊ ትልቅ ቦታ ላይ ባለ ሰው አይመኩም፡፡ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር በመስጠት፣ እስከ ዛሬ ለእኛ ለሕይወታችን ትምህርት የሚሆን ተግባር አሳይተውናል፡፡

ይህም በተለይ ለእኔ ለግሌ፣ ምንም ያህል ፈተናዎች፣ መከራዎችና ጭንቀቶች ቢበዙም፣ ሁሉንም ለእግዚአብሔር አሳልፎ ከመስጠት የተሻለ መፍትሔ እንደሌለ በተግባር አስተምሮኛል፡፡ የማኅበሩ አገልጋዮች ምንም ዓይነት ችግር ቢገጥማቸው፣ በጋራ በመጸለይ ነበር ችግሩን የሚወጡት፡፡ በተለይም በወቅቱ በተከታታይ ይገጥሙ የነበሩ ፈተናዎችን ሁሉ ለማለፍ በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ይደረግ የነበረው የፈተና መውጫ መንገድ፣ ዛሬም ድረስ ለእኔ ትልቅ ትምህርት ነው፡፡ በጣም ከባድ ፈተና ሲደርስባቸው፣ ያንን ፈተና በወረቀት ጽፈው ለመ/ል/ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በመስጠት ‘ቅዱስ ማርቆስ ሆይ! አንተ ፍታው’ ብለው እንዲጸለይበትና እንዲቀደስበት በማድረግ ፈተናዎቹን ያልፏቸው ነበር፡፡

<<...አሁንም በፍጹም ልቡናህ ጨክነህ ንስሓ ግባ...>>(፪ኛ መቃ ፫፥፯)

ንስሓ ማለት አንድ ክርስቲያን ከክርስትና ጥምቀት በኋላ በድካም ወይም ባለማወቅ ለፈጸመው ኃጢአት በፈጣሪው ፊት ቀርቦ የሚጸጸትበት፣ ዳግመኛ ያን ኃጢአት ላለመሥራት ወስኖ በመናዘዝ ከእግዚአብሔር ጋር የሚታረቅበትና የነፍስ ፈውስ የሚያገኝበት ታላቅ ምሥጢር ነው። የሰው ልጅ ከኃጢአት ያለ ንስሓ ንጹሕ ሊሆን ስለማይችል ንስሓ የሌለበት ሕይወት መጨረሻው ጥፋት ነው።

ንስሓ በስሜታዊነት የምንገባው ሳይሆን በፍጹም ጸጸት፣ በመመለስና በማመን በካህኑ አማካይነት በእግዚአብሔር ፊት የምንፈጽመው ከኃጢአት፣ ከበደል፣ ከዲያብሎስ እስረኝነት የምንላቀቅበትና የምንነጻበት ድንቅ ምሥጢር ነው። ተወዳጁ ሐዋርያ ቅዱስ ዮሐንስ በመልእክቱ "**ኃጢአት የለብንም ብንል ግን ራሳችንን እናስታለን፤ የቀና ነገርም በእኛ ዘንድ የለም።**" (፩ኛ ዮሐ ፩፥፰) ብሎ እንደነገረን ከበደል ነጻ ነን በማለት ራሳችንን ማታለል ለንስሓ እንዳንበቃ ያደርገናል፤ ሰው ከገቢር ኃጢአት ቢጠበቅ ከነቢብ አይነጻም፣ ከነቢብ ቢጠበቅ ከኀልዮ ኃጥአት  አይነጻምና ንስሓ ለሰው ልጅ መሠረታዊ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኛ ድልድይ ነው።

እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ሰዎች በንስሓ ወደእርሱ እንዲመለሱ ጥሪ በማድረግ ይጠባበቃል፤ ፈቃዱንም እንድናደርግ እርሱም ምሕረቱን ሊያወርድልን መልካምና በጎ ፈቃዱ ነው፤ "**ወደ እግዚአብሔር ተመለስ፥ ኃጢአትንም ተዋት፤ በፊቱም ጸልይ፤ ለበደልህም ንስሓ ግባ፤ ከበደልህም ወደ እግዚአብሔር ተመለስ፤ ኃጥአትን ሁሉ ጥላ፤ ፈቃዱንም አድርግ።**" (ሲራክ ፲፯፥፳፭-፳፮) በማለት ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚነግረን በንስሓ ሕይወት የመኖር ጥበብን ገንዘብ አድርጎ ወደ እግዚአብሔር በመመለስ በፈቃዱ መመላለስ ምሕረቱን ቸርነቱን ያጎናጽፋል።